በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የተመደበለትን የመደበኛ ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩንቨርስቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩንቨርስቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩንቨርስቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

1. በዩኒቨርስቲው የመስተንግዶ አገልግሎት በድምሩ ብር 629,897.70 ያለውድድር በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፣
2. በመስክ ላልነበሩ የመስክ ስራ እንደቆዩ ሆኖ በመፈረምና በሚመለከተውም ኃላፊ ተረጋግጦ በድምር ብር 96,379.55 ለውሎ አበል የተከፈለ መሆኑ፣
3. በዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራሮች ውሳኔ መሠረት የኮማንድ ፖስት አባላት ስብሰባ በሚያደርጉበት ጊዜ እና ለሹፌሮች ለቅዳሜና እሁድ ስራዎች የቁርስ የምሳ እና የእራት እንዲከፈላቸው በተወሰነው መሰረት በድምር ብር 45,500.00 የትራንስፖርትና የውሎአበል በሚል የተከፈለ መሆኑ፣

4. ሹፌሮች የትርፍ ሰዓት ለሚሰሩበት ቁርጥ አበል እንዲከፈላቸው ከተወሰነው እና ከተፈቀደው አበል በተጨማሪ የ60 ሰዓት ትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር **72,808.44** ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣
5. ዩኒቨርሲቲው በፕሳ 9 ለተፈቀዱ የስራ መደቦች የአካዳሚክ ባለሙያዎችን በመመደብና ለአካዳሚክ ዳይሬክተሮች የተፈቀደውን የሀላፊነት አበል፣ አኑዋላይዜሽን እና የቤት አበል ለስራ መደቡ ያልተፈቀደውን እንዲከፈሉ በመደረጉ ያልተጣራ ብር 343,857.50 የተጣራ ብር **223,507.00** ከመመሪያ ውጭ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣
6. የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ባደረገው ስብሰባ ለተማሪ ፖሊሶች ለእያንዳንዳቸው በየወሩ የ400 ብር የስልክ ካርድ ተገዝቶ እንዲሰጣቸው በወሰነው መሰረት በድምሩ ብር **96,750.00** የተከፈለ መሆኑ፣
7. የሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ውድድር አሸናፊ ለሆኑትና ለተወዳደሩት ተማሪዎች ማበረታቻ በሚል ብር **76,000.00** ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣
8. የዩኒቨርሲቲው ኤክስኪቲቭ ማኔጂመንት ካውንስል ለተቋሙ ዋና ገንዘብ ያዥ ብር 300.00 እንዲሁም ለረዳት ገንዘብ ያዥ ብር 200.00 የካዝና መጠባበቂያ ክፍያ ከውስጥ ገቢ የሚታሰብ ሆኖ በየወሩ እንዲከፈላቸው በመወሰኑ ብር **2,400.00** የተከፈላቸው መሆኑ፣
9. በጠቅላላው ብር **393,760.00** የክፍያው መጠን (Rate) በሚመለከተው የመንግሥት አካል የተፈቀደበት ማስረጃ ያልቀረበለት እና ስራው ለመስራት ውል የገቡበት ማስረጃ ከወጪ ማስመስከሪያው ጋር ያልቀረበ መሆኑ፣
10. የቀረበው ደረሰኝ ከመኪና አከራይ ድርጅት ያልሆነና ደረሰኝ የሌላቸው በሚል በድምሩ ብር **18,775.00** ለተከፈለው የክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ ፣
11. ለላየን ሴኩሪቲና የፅዳት አገልግሎት ሀ/የተ/የግ/ማህበር በ2008 በጀት ዓመት ለተሰራ ስራ በጀት ዓመቱን ሳይጠብቅ በ2009 በጀት ዓመት ብር **715,204.00** ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣
12. በዩኒቨርሲቲው ከተቀጠሩ የውጭ ሀገር መምህራን፣ ከዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ባለሙያዎች፣ ከአካዳሚክ ባለሙያዎች እና ከዩኒቨርሲቲው እና ከውጭ ባለሙያዎች ሊቀነስ የሚገባው የስራ ግብር በድምሩ ብር **2,954,942.26** ሳይቀነስ የተገኘ መሆኑ፣
13. ዩኒቨርሲቲው ብር **1,016,203.37** ከውስጥ ገቢ መክፈል የሚገባውን ከመደበኛ በጀት ለተከታታይ ትምህርት ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣

14. በድምሩ ብር 12,687,847.63 ወጪዎች በተገቢው የሂሳብ መደባቸው ሳይመዘገቡ የተገኙ መሆኑ፣
15. የዩንቨርሲቲው መምህራኖች ከተፈቀደላቸው የትራንስፖረት አበል በተጨማሪ የሰርቪስ ትራንስፖረት አገልግሎት በመሰጠቱ እና ከተደረገው የመኪና ኪራይ የውል ስምምነት ውጭ ቅዳሜና እሁድ ፈተና ለሚፈትኑና ለስብሰባ (ለውይይት) በሚል ለመምህራን የትራንስፖርት አበል እየተከፈላቸው በተጨማሪ ሰርቪስ ተመድቦ በድምሩ ብር 2,051,468.00 ለአገልግሎቱ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣
16. በዩኒቨርሲቲው በዕቅድ ያልተያዘ እና በጀት ያልተፈቀደለት የኮንትራት መያዣዎች ሂሳብ በድምሩ ብር 1,212,589.70 በሂሳብ መደብ 5061 በወጪ ተይዞ ለተለያዩ የህንፃ ተቋራጮች ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣
17. በድምሩ ብር 27,592,730.23 በዩኒቨርስቲው የግንባታ ጽ/ቤት መሀንዲስ እና በህ/ሥ/ተቋራጮች በተዘጋጀ የክፍያ ሰርተፍኬት እና በሥራ አመራሩ ፀድቆ እንዲከፈል የተደረገ መሆኑ፣
18. የዩኒቨርስቲው ኢንጅነሪንግና የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከሚመለከተው ክፍል የተሰጠ አማካሪ መሃንዲስ ለመሆን የሚያስችል የስራ ፍቃድ ሳይኖረው በስራ ተቋራጮች መከናወን የሚገባቸው ብር 154,766.67 ዋጋ ያላቸው ፕሮጀክቶች የማማከር፣ ዲዛይን የመስራት፣ ጨረታ የመገምገም ሥራዎች ያከናወነ መሆኑ፣
19. በዩኒቨርሲቲ ስር የሚገኙት ተሽከርካሪዎች በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተጠቀሙት የነዳጅ መጠንና ከሸፈኑት የኪ/ሜትር ርቀት በየወሩ ምዝገባ እየተከናወነ ተገቢው ሪፖርት ከጠቅላላ አገልግሎት እንዲቀርብ ተጠይቆ በቀረበው ማስረጃ መሰረት በጠቅላላው ከሾፌሮች 13,095.27 ሊትር ነዳጅ በጉድለት የሚፈለግ መሆኑ፣
20. ብር 5,809,058.61 ተሰብሳቢ ሂሳብ እስከ 2009 በጀት ዓመት መጨረሻ መወራረድ ሲገባው ያልተወራረደ መሆኑ፣
21. በመክፈቻ ሂሳብ /Opening balance/ በተሰብሳቢ ሂሳብ በተለያዩ ተቀጽላ ቋት /ሌጀሮች/ ብር 11,129,206.79 አግባብ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን ክሬዲት ሂሳብ የሚታይ መሆኑ፣
22. የውሎ አበል እና በሚያቀርቡት ህጋዊ ደረሰኝ የሚወራረድ የአምስት ቀን የአልጋ ኪራይ ከውሎ አበል በተጨማሪ (በቀን አስከ ብር 500.00 የሚደርስ) ብር 2,500.00

እንዲሰጣቸው በመደረጉ የአልጋ ኪራይ ያለ አግባብ ብር 40,000.00 የተከፈለ እና በበጀት ዓመቱ ያልተወራረደ መሆኑ፣

23. ብር 1,874,046.93 ተከፋይ ሂሳብ እስከ 2009 በጀት ዓመት መጨረሻ መከፈል ሲገባው ያልተከፈለ መሆኑ፣

24. በመክፈቻ ሂሳብ /Opening balance/ በተከፋይ ሂሳብ በተለያዩ ተቀጽላ ቋት /ሌጀሮች/ ብር 2,379,927.89 አግባብ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን በዴቢት የሚታይ መሆኑ፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር ከ1 እስከ 24 በተገለጹት ጉልህና በሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርስቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳይም፡፡

ሌሎች ጉዳዮች፣

1. ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት፣
   - ለመደበኛ (1800) ወጪ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ መደቦቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር 100,123,961.82 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤
   - ከውስጥ ገቢ (1900) ወጪ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ መደቦቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር 14,553,637.00 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤
   - ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ መደቦቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር 258,459,726.48 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤
2. **ንብረት፣**
   - በተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ዕቃዎችን መቆጣጠሪያ ካርድ (UC) ለተጠቃሚዎች ያልተሰጠ መሆኑ፣
   - ለቋሚ ዕቃዎቹ መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፣
   - ዩኒቨርሲቲው በስጦታ የተቀበላቸው መኪናዎች ሠ.ቁ 4-21229፣ 4-15080 በባለሙያ ዋጋቸው ያልተተመነ መሆኑ፣
   - የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ የተደረገው በዕቃ መጋዘን (ስቶር) ውስጥ ያሉትን ብቻ እንጂ በየቢሮው ያሉ ቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ ያልተደረገላቸው መሆኑ፣

- በተማሪዎች ምግብ ቤት ንብረት ክፍል ውስጥ አገልግሎታቸው ያለፈባቸው ብዛታቸው 916 ጣሳ የሚሆኑ ማርማራታ መኖራቸው፣ በተጨማሪም የተበላሹ የምግብ አቅርቦቶች /ብጣሪዎች/ መኖራቸው፣
- በቋሚ ዕቃዎች ግምጃ ቤት የቋሚ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እና የንብረት ወጪ ደረሰኝ በአንድ ሰው የሚዘጋጅ መሆኑ፣
- በተማሪዎች ምግብ ማብሰያ ክፍል ውስጥ ባለ አራት የምግብ ማብሰያዎች (ኩኪንግ ማሽን ወይም እስቶፍ) ብዛት 21፣ የዳቦ ማቡኪያ ማሽን 2 ጥገና ሳይደረግላቸው ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆናቸው፣
- የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድሃኒቶች ከ2 ዓመት በላይ ሳይወገዱ በመፀዳጃ ቤት ውስጥ እንዲቀመጡ መደረጉን፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ወደ 75 የሚሆኑ ዲስክ ቶፕ ኮምፒተሮች ሳይወገዱ ከሁለት ዓመት በላይ በቋሚ ንብረት ክፍል ውስጥ ተቀምጠዉ መገኘታቸው፣
- የመለዋወጫ ዕቃው መለያ ቁጥርም በተሽከርካሪው የግል ማህደር ውስጥ ተመዝግቦ እንዲቀመጥ መደረግ አለበት፤ ቢልም ገቢ የሚደረገው /የተቀየረው/ ንብረት ቀደም ሲል በንብረት ክፍል ከተመዘገበው መለያ ቁጥር ጋር የማይመሳከር መሆኑና አዲስ የተለወጠው መለያ ቁጥር የማይመዘገብ መሆኑ፣

3. <u>ልዩ ልዩ፣</u>

- በዩኒቨርስቲው የሚገኙ ግንባታዎች በመዝገብ ያልተመዘገቡ መሆኑ፣
- የዩንቨርስቲው ግንባታዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ መሆኑ፣
- ዩንቨርስቲው የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ፣ የተጋላጭነት ደረጃ መለየት እና የሥጋት ተጋላጭነት ፍተሻ ያላደረገ መሆኑ፣
- በዩንቨርስቲው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ሲታይ፡-
    - የመረጃ ደህንነት አስተዳደር /approved IT security policy to ensure data confidentiality, integrity and availability/ የሌለ መሆኑ፣
    - የአይ ሲቲ ቀጣይነት እና የመልሶ ማቋቋም ዕቅድ /disaster recovery plan/ የሌለ መሆኑ፣

- ለዩኒቨርሲቲው በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደባቸው፣
    - ከተለያዩ ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች የተፈፀመው ግዥ በግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት አዘግይተው ላቀረቡ ድርጅቶች ቅጣት ሳይፈፀም ብር 332,443.84 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣
    - ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች መኝታ አገልግሎት የሚውል የብረት ቁም ሳጥን ለመግዛት ጨረታ ያወጣ ቢሆንም በጨረታው ሰነድ ላይ ከተገለጸው ስፔሲፍኬሽን ውጭ በብር 4,485,000.00 የእንጨት ቁም ሳጥን ግዥ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

መግቢያ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን መሰረት የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርስቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፣

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርስቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ፣ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የተቋሙ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. **የወጪ ሂሳብ፣**

1.1.1 **ግኝት፣ በዋጋ ማወዳደሪያ መገዛት ሲገባው በቀጥታ ግዥ የተፈፀመ፣**

የዩንቨርሲቲው የግዥ ሂደት በፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ታህሳስ 1/2008 ዓ.ም ክፍል 9 አንቀጽ 25(7) (ሀ) የመንግስት መ/ቤት በግዥ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ዋጋቸው ከብር 5,000.00 ያልበለጠ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ወይም በጉዞ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከመፍታት ጋር የተያያዙ የቀጥታ ግዥዎችን ከማናቸውም ሻጭ ድርድት መፈፀም ይችላል፡፡ ሆኖም በዚህ ዓይነት የሚፈፀሙ ጥቃቅን ግዥዎች ድምር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከብር 75,000.00 መብለጥ አይኖርበትም ይላል፡፡ ይሁን እንጂ በዩኒቨርስቲው የመስተንግዶ አገልግሎት በድምሩ ብር 629,897.70 ያለውድድር በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የድርጅቱ ስም	የወጭ ማስመስከሪያ ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የገንዘብ መጠን
1	29/10/09	ፒራሚድ ሆቴል-ደ/ዘይት	673332	6233	44,555.93
2	22/10/09	ፒራሚድ ሆቴል	673203	6233	49,057.68
3	28/10/09	ክራውን ሆቴል	673158	6233	58,397.71
4	05/10/09	ክራውን ሆቴል	673408	6233	53,223.58
5	10/12/08	ከትዕግስት፣ሰብለ እና መአዛ የምግብ ዝግጅት /ሽርክና/ ማህበር	0640607	6233	242,615.50
6	18/02/09	›› ›› ››	0830911	6233	182,047.30
				ድምር	**629,897.70**

1.1.2 <u>ስጋት፤</u>

- በውድድር ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም ሊያሣጣ ይችላል፡፡
- በግዥ መመሪያ መሠረት ግዥ ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት ይህም ቁጠባን ፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም
- የመንግሥትም ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

1.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ግዥዎች ሲፈፀሙ ተገቢውን የመንግስትን አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም እንዳይከሰት ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.1.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- የሆቴል መስተንግዶ በተመለከተ ያለውድድር መካሄዱ ስህተት መሆኑን ተቀብለናል፡፡ ለወደፊቱ እናስተካክላለን፡፡
- ለመስተንግዶ አገልግሎት በሰብለና መአዛ ም/ዝግጅት የቀረበ አግልግሎት የመንግስት የግዢ ሂደት አልተከተለም በሚል የተያዘው ዩንቨርስቲው የተማሪዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ የነበረው የውሀ አቅረቦት እንዲያቀረቡ ዩንቨርስቲው ባቋቋማቸዉ የመስተንግዶ ኮሚቴ ተዋቅሮ በግቢዉ ወስጥ ያሉትን አቅረቦ በአካል በማነጋገር ዝቅተኛ ዋጋ ሰብለና ማአዛ እንዲያቀረቡ ተለይቶ ከነዚህ አቅራቢዎች በፋብሪካ ዋጋ በማቅረብ አሸናፊ ሆነዉ ያቀረቡት በመሆኑ በግልፅ ጨረታ ወይም በውስን ጨረታ አለማድረጋችን ተቀብለናል፡፤ ለወደፊት የምናስተካክለዉ ይሆናል፡፡

በማለት ገልፀዋል፡፡

1.2.1 <u>ግኝት፣</u> <u>በመስክ ላልነበሩ የተከፈለ የውሎ አበል፣</u>

- የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል መመሪያ ሰኔ 2004 ዓ.ም ክፍል 2 አንቀጽ 4 የውሎ አበል ተመንና አከፋፋል መሰረት ኦዲት ሲደረግ፣ ባለሙያዎቹ በመስክ ስራ ላይ ሳይሆኑ የመንግስት ሰራተኞች ውሎ አበል ክፍያ ማወራረጃ ቅጽ 2 ለኦዲት በተመረጡ የወጭ ማስመስከሪያዎች ያለ አግባብ የመስክ ስራ እንደቆዩ ሁኖ በመፈረምና በሚመለከተውም ኃላፊ ከህግ ውጭ የሚያረጋገጥ በመሆኑ ብር 88,843.55 የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣

- ተማሪዎች ወደ ተለያዩ ቦታዎች በሚሄዱበት ጊዜ አብረው የሚሄዱ መምህራኖች የሚሄዱትም ይሁን የሚመለሱት ከተማሪዎች ጋር ቢሆንም ባለሙያዎቹ ተማሪዎቹ ከቆዩበት ቀን በላይ በመስክ ስራ ላይ እንደሆኑ የመንግስት ሰራተኞች ውሎ አበል ክፍያ ማወራረጃ ቅጽ 2 በመሙላትና የሚመለከከተውም ኃላፊ በማረጋገጥ ያለ አግባብ ብር 7,536.00 ተከፈሎ የተገኘ መሆኑ፣

በድምሩ ብር 96,379.55 አለአግባብ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

1.2.2 ስጋት፣

- በመመሪያ መሰረት ክፍያ ካልተፈፀመ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡
- በመስክ ስራ ላይ ሳይሆኑ ፎርም መሙላትና አበል መውሰድ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- በመስክ ስራ ያልነበረን ባለሙያ የመስክ ስራ ነው ብሎ መፈረምና ማረጋገጫ መስጠት ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል

1.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ ክፍያ መፈፀም ይገባል፡፡
- ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች ተመላሽ ሊደረጉ እና ለወደፊትም ጥንቃቄ ሊወሰድ ይገባል፡፡

1.2.4 የስራአመራሩ ምላሽ፣

- ለመምህራን በተማሪዎች ልክ ያልተከፈለበት ምክንያት ተማሪዎች ኢንተርሽፕ ወይም የመስክ ጉብኝት የሚቆዩበት ለውስን ቀናት የሚቆዩ ሲሆን፣ መምህራኖቹ ግን ተማሪዎች ከመግባታቸው በፊት ቀድመው ስለሚሄዱና ተማሪዎች ከተመለሱም ቆይተው ስልጠናውን ከሰጡት ድርጅቶች ጋር ውይይት ስለሚያደርጉ ለቀጣይም ፕሮግራም ለማስያዝ ያመች ዘንድ የሚቆዩበት ሁኔታ አለ በዚህ መሰረት ከተማሪዎች የተለየ ክፍያ ይወስዳሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከቆይታ ውጭ የተከፈላቸው ካሉ እያጣራን የምናስመልስ ይሆናል ፡፡
- ያለአግባብ የተወሰደ አበል መሆኑን አጣርተን በብልጫ የተወሰደውን ክፍያ የማስመለስ ስራ እንሠራለን ፡፡

በማለት ገልፀዋል፡፡

1.3.1 ግኝት፣ የኮማንድ ፖስት እና የሹፌሮች የውሎ አበል ክፍያ በተመለከተ፣

- በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የመንግስት ሰራተኞች የአገር ውስጥ የውሎ አበል ክፍያ አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 8 የውሎ ገብ አበል አከፋፈል ቁጥር አንድ ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ለስራ ጉዳይ ከመደበኛ የሥራ ቦታው ውጭ ወደ ሌላ የስራ ቦታ ሲንቀሳቀስ (ሀ) ከአንድ ሰዓት በፊት የሚንቀሳቀስ ከሆነ ለቁርስ ይታሰብለታል፡፡ (ለ) ሄዶ ዕለቱን ከሰድስት ሰዓት ተኩል በኃላ የሚመለሰ ከሆነ ለምሳ ይታሰብለታል፡፡ (ሐ) ሄዶ ምሽቱን ከሁለት ሰዓት በኃላ የሚመለስ ከሆነ ለእራት እንደሚታሰብለት መመሪያው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራሮች ውሳኔ መሠረት የኮማንድ ፖስት አባላት ስብሰባ በሚያደርጉበት ጊዜ በቀን ብር 200.00 የትራንስፖርት አበል በሚል ከደንብና መመሪያ ውጭ በ21/02/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 129236 ብር 9,400.00፣ በ28/05/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 128523 ብር 12,800.0 እና በ20/04/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 128511 ብር 11,800.00 በድምሩ ብር 34,000.00 ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣
- የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር በ22/06/08 ባደረገው ስብሰባ ለሹፌሮች ለቅዳሜና እሁድ ስራዎች የቁርስ የምሳ እና የእራት እንዲከፈላቸው መወሰኑን በመግለጽ በ28/06/2008 ዓ.ም በቁጥር አአሳቴዩ/1006/5590/08 ዓ.ም ከአስተዳደር ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ለፋይናንስ አስተዳደር በማሳወቁ ከመመሪያ ውጭ ያለአግባብ በ20/04/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 128510 ብር 11,500.00 ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣

በድምሩ ብር 45,500.00 አላግባብ የውሎ አበል ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

1.3.2 ስጋት፣

የመንግስትን ገንዘብ ከደንብና መመሪያ ውጭ መጠቀም የመንግስት መመሪያን ከመጣሱም በላይ ለምዝበራና ለብክነት ሊያጋልጥ ይችል ይሆናል፡፡

1.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ከመንግስት የክፍያ መመሪያና ደንብ ውጭ የሚከፈል ማናቸውም ክፍያዎች ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ከመመሪያ ውጭ አለአግባብ የተከፈለው ክፍያ ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

1.3.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

- የኮማንድ ፖስት ለዩኒቨርሲቲው ጸጥታና ደህንነት መጠበቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስላለው የኮማንድ ፖስት አባላት በተሰበሰቡ ጊዜ ብቻ ለምሳና ትራንስፖርት እንዲሆን በሚል ብር 200 በማኔጅመንት ደረጃ ተነጋግረን ወስነን ከፍለናል ይህም አባሎችን ተነሳሽነት የሚጨምር እንደሚሆን በማመን ነበር ነገር ግን ይህ ክፍያ ሙሉ ለሙሉ እንዲቆም ተደርጓል፡፡
- ለሾፌሮች ቅዳሜና እሁድ ቁርስ ምሳና እራት አበል የሚከፈለው ዩኒቨርሲቲያችን ከከተማ የራቀና በተደጋጋሚ ለስራ ፈላጊዎች ማስታወቂያ ቢወጣም ብቁ ተወደዳዳሪ ባለማግኘታችን ያሉትን ሾፌሮች ከስራው ስፋት አንፃር በማናቸውም ጊዜ በትርፍ ሰአታቸው ስለሚሰሩ ቅዳሜና እሁድን ሰርተው ክፍያ ካልፈጸምን አገልግሎታቸውን ማግኘት የማንችል በመሆኑ ማኔጅመንቱ ተወያየቶበት ክፍያ ሲፈጸም ቆይቷል ነገር ግን ይህ ኦዲት ግኝት ከተነገረን ከጥር ወር 2009 ጀምሮ አቁመናል ፡፡

በማለት ገልፀዋል፡፡

1.4.1 ግኝት፣ አለአግባብ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣

የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ.30/ጠ13/49/1056 በ19/05/2007 ዓ.ም ከመደበኛ የስራ ጊዜያቸው ውጭ ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ በዘላቂነት አገልግሎት መስጠት በሚያስገድዱ ለሚሰሩ ሹፌሮች የትርፍ ሰዓት ክፍያ መክፈሉ አዋጭ አለመሆኑን በመግለጽ የትርፍ ሰዓት ለሚሰሩበት ቁርጥ አበል እንዲከፈላቸው አሳውቋል፡፡ በዚህም መሰረት ዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፣

- ከተፈቀደው አበል በተጨማሪ የ60 ትርፍ ሰዓት ክፍያ የሚከፈላቸው በመሆኑ አለአግባብ ብር 72,808.44 ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣

1.4.2 ስጋት፣

- በመንግስት የሚወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡
- የመንግስት ገንዘብ ያለ አግባብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡

1.4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- የሚከፈሉ ክፍያዎች ስልጣን በተሰጠው አካል የተፈቀዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

- ያለ አግባብ የተከፈለው የትርፍ ሰዓት ክፍያ መቋረጥ እና ገንዘቡም ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.4.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- በተሰጠው የኦዲተር አስተያየት ከጥር ወር 2009 ጀምሮ ምንም ዓይነት ክፍያ አልተፈፀመም ብለዋል፡፡

1.5.1 <u>ግኝት፣ አለአግባብ የተከፈለ የሀላፊነት ፣ ኡኑዋላይዜሽን እና የቤት አበል፣</u>

በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 መሰረት ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ሠራተኞች የደመወዝ መጠንና ጥቅማ ጥቅም ቀርቦ የሚወሰነው በሚንስትሮች ምክር ቤት መሆኑ የተደነገገ ሲሆን፣ በተጨማሪም የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/03 ባስተላለፈው መመሪያ ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ /በቦርዱ/ የሰራተኞችን የደመወዝ መጠን ማሻሻል፣ መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና እስከ አሁን የተከናወኑም ካሉ ትክክል እንዳልሆነ የተወሰነ መሆኑ እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ መጠን እና ጥቅማ ጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ አሳውቋል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በፐሳ 9 ለተፈቀዱ የስራ መደቦች የአካዳሚክ ባለሙያዎችን በመመደብና ለአካዳሚክ ዳይሬክተሮች የተፈቀደውን የሀላፊነት አበል፣ አኑዋላይዜሽን እና የቤት አበል ለስራ መደቡ ያልተፈቀደውን እንዲከፈሉ በመደረጉ ያልተጣራ ብር 343,857.50 የተጣራ ብር 223,507.00 ከመመሪያ ውጭ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

1.5.2 <u>ስጋት፣</u>

- መንግስት በተለያየ ጊዜ የሚያወጣቸው አዋጆችና መመሪያዎች ተግባራዊ ላይደረጉ ይችላሉ፡፡
- የመንግስት ውስን ሀብት ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡
- ከህግ እና መመሪያ ውጭ የሆኑ ውሳኔዎችን በመወሰን የሚከፈል ክፍያ ተጠያቂነት ሊያመጣ ይችላል፡፡

1.5.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ቦርድም ሆነ የዩኒቨርሲቲው ስራአመራር የተለያዩ ውሳኔዎችን ሲወስን መንግስት በተለያየ ጊዜ የሚያወጣቸው አዋጆችና መመሪያዎችን የተከተለ ሊሆን ይገባል፡፡
- ለስራ መደቡ በተፈቀደው መሰረት ባለሙያዎችን መቅጠር ካልሆነም በአካዳሚክ ባለሙያዎች እንዲያዝ ከተፈለገም በሚመለከተው አካል መዋቅሩን ማስፈቀድ ይገባል፡፡
- በመከፈል ላይ ያሉ ክፍያዎች በመመሪያ ያልተደገፉ በመሆኑ ክፍያው እንዲቆም ተደርጎ እስከ አሁን ያለ አግባብ የተከፈለው ክፍያ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.5.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- በኦዲት ግኝት የታዩት የሥራ መደቦች ከፍተኛ ሙያና ብቃት የሚጠይቁ እንዲሁም ልዩ የስራ ልምድ ያለው ባለሙያ የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ ቦታውን ለመሸፈን በፕሳ 9 በተደጋጋሚ የቅጥር ማስታወቂያ ቢወጣም ብቃት ያለው ሰው አልተገኘም፡፡ ሌሎቹ ደግሞ በመሰረቱ በአስተዳደር ሰራተኛ ሳይሆን በአካዳሚክ ባለሙያ መሰራት ያለባቸው ሲሆን በስህተት በመዋቅሩ ላይ የወጡ ናቸው፡፡ /ለምሳሌ ስርዓተ ጾታ-ዳይሬክቶሬት፣ የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣ ተቋማዊ ለውጥና መልካም አስተዳደር/ በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው የመማር ማስተማር፣ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ስራውን በብቃት ይወጣ ዘንድ የተጠቀሱትን ቦታዎች ለቦታው ብቁ የሆኑ መምህራንን በስራቸውና በስነምግባራቸው የተሻሉትን አወዳድሮ በመመደብ በመደበኛነት ከተቀጠሩበት ስራ በተጨማሪ እንደሌሎቹ የአካዳሚክ ዳይሬክተሮች የቢሮዎችን ስራ በአጥጋቢ ሁኔታ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ በስህተት ፕሳ 9 የሆኑትን ቦታዎች ከሚመለከተው ክፍል ጋር በመነጋገር እንዲስተካከል የምናደርግ ሲሆን በፕሳ 9 የተመደቡትን ሌሎች ሌሎች ቦታዎችን ግን አሁንም በአስተዳደር ሰራተኛ በቅጥር ስናገኝ የምንተካና የምናስተካክል መሆኑ እንዲታዎቅልን እየገለጽሁ የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካትና የመንግስት ሀብትን በአግባቡ ለመጠቀም አበክረን የምንሰራ መሆናችንን እንገልፃለን ብለዋል፡፡

1.6.1 ግኝት፣ ለተማሪ ፖሊስ የተከፈለ የሞባይል ካርድ፣

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በ13/8/03 በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 ባስተላለፈው መመሪያ ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ /በቦርዱ/ የሠራተኞችን የደመወዝ ስኬል ማሻሻል፣ መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና እስከአሁን የተከናወኑም ካሉ ትክክል እንዳልሆነ የተወሰነ መሆኑ እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ ስኬሎች እና ጥቅማጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ ያሳሰበ ቢሆንም፤

- የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር በ12/10/09 ባደረገው ስብሰባ ለ82 የተማሪ ፖሊስ የግንቦትና የሰኔ ወር 2009 ዓ.ም ለእያንዳንዳቸው በየወሩ የ400 ብር የስልክ ካርድ ተገዝቶ እንዲሰጣቸው ወስኗል፡፡ በዚሁም መሰረት በ15/10/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0673516 ብር 65,550.00 በሂሳብ መደብ 6258 ተመዝግቦ ወጪ የተደረገ መሆኑ እና በ01/06/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 427523 ብር 33,200.00 ለተማሪዎች ፖሊስ የሞባይል ክፍያ በሚል ወደሳጥን ከመጣ በኋላ በ26/06/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣያ ቁጥር 128661 በሂሳብ መደብ 6231 ለ78 የተማሪ ፖሊስ ብር 31,200.00 ከመመሪያ ውጭ መከፈሉ፣ በድምሩ ብር 96,750.00 አላግባብ ከውስጥ ገቢ የተከፈለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

1.6.2 ስጋት፣

በመመሪያ ያልተደገፈ ክፍያ መፈጸም ለመንግስት ገንዘብ ምዝበራ መንስኤ ከመሆኑም በላይ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

1.6.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ለተማሪ ፖሊስ የሞባይል ካረድ ክፍያ በሚል የሚፈፀመው ክፍያ በአስቸኳይ እንዲቆም፤ አላግባብ የተከፈለውም የመንግስት ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ፡፡ ጉዳዩ ለዩኒቨርስቲው አስፈላጊ ለመሆኑ ከታመነበት የሚመለከተውን አካል በማስፈቀድ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተመሣሣይ ሁኔታ እንዳይከሰት የስራ አመራሩ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.6.4 የስራአመራሩ ምላሽ፣

በዩኒቨርሲቲው ያቋቋምናቸው የተማሪ ፖሊሶች ከግቢው የፀጥታና ደህንነት ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር የግቢውን ፀጥታ እንዲሁም የተማሪዎችን ደህንነት

የማስጠበቅ ስራ የሚሠሩ አካላት ናቸው፡፡ ለነዚህም ተማሪዎች በማናቸውም ጊዜ በ24 ሰዓት ከተጠቀሰው ዳይሬክቶሬት ጋር የስልክ ግንኙነት ያደርጋሉ፡፡ ስለዚህ ለዚህ ግንኙነት እንዲረዳ በሚል በወር 400 ብር የሞባይል ካርድ ሲሠጣቸው እንደነበር እየገለጹን ይሁንና የኦዲት ግኝት አግባብነት የለውም ከተባለ ጀምሮ ክፍያው እንዲቆም ተደርጓል፡፡ የታረመ ችግር ነው ለወደፊቱም አይደረግም በማለት ገልፀዋል፡፡

1.7.1 <u>ግኝት</u>፣<u>አለአግባብ የተከፍለ የማበረታቻ ክፍያ</u>፣

በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 መሰረት ክፍል ሁለት አንቀጽ 11/2 ኤጀንሲው የልዩ ልዩ የአበል ዓይነቶችን እና ክፍያዎችን እያጠና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡ እንዲሁም ሲፈቀድም አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል ብሎ ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/03 ባስተላለፈው መመሪያ ላይ በስራ አመራር ቦርድ የሚመሩ አንዳንድ የከፍተኛ ትምህርት እና ሌሎች ተቋማት ከመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ውጪ የሰራተኞችን ደመወዝ፣ ጥቅማ ጥቅሞች ለሰራ አመራር ቦርድ እያቀረቡ በማስወሰን ተግባራዊ ማድረጋቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ጉዳዩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በ4ኛው የምርጫ ዘመን 15ኛው መደበኛ ስብሰባ ላይ ተነስቶ ውይይት ከተደረገ በኃላ ከጠቅላይ ሚኒስትር ፈቃደ ውጭ ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ /በቦርዱ/ የሰራተኞችን የደመወዝ መጠን ማሻሻል፣ መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና እስከአሁን የተከናወኑም ካሉ ትክክል እንዳልሆነ የተወሰነ መሆኑ እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ ስኬሎች እና ጥቅማጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ ሲል በጥብቅ አሳስቧል፡፡ በዚህም መሰረት ለአስተዳደር ሰራተኞች የተከፈሉ ጥቅማ ጥቅሞችን ኦዲት ሲደረግ፣ ዩኒቨርሲቲው በ12/10/2009 በአካደሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት ለፋይናንስ አስተዳደር ዳሬክቶሬት በተፃፈው ደብዳቤ ከግንቦት 10-11 2009 በተካሄደው 3ኛዉ ዓመታዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ውድድር አሸናፊ ለሆኑትና ለተወዳደሩት ተማሪዎች በሚል በ20/10/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 128542 ብር 76,000.00 በሂሳብ መድብ 6417 ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

1.7.2 ስጋት፣

የመንግስት ገንዘብ ለታለመለት ዓለማ እንዳይውልና የክፍያ መመሪያዎች እንዲጣሱ እንዲሁም ውስን የመንግስት በጀት ያለአግባብ እንዲባክን በር ሊከፈት ይችላል፡፡

1.7.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ፈቃድ ውጭ ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ /በቦርዱ/ የሰራተኞችን ጥቅማ ጥቅሞች መፍቀድ አይችልም፡፡ በመሆኑም አለአግባብ የሚከፈለው ማበራታቻ እንዲቆም እና ለወደፊቱም ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ከላይ በተላለፈው መመሪያ መሰረት የሚመለከተውን አካል ጠይቆ ሲፈቀድለት ብቻ ክፍያም ሆነ ጥቅማ ጥቅሙ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

1.7.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ዩኒቨርሲቲያችን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተቋም መሆኑ ይታወቃል፡፡ ተማሪዎችም ሲማሩ የሚፈጥሯቸው የተለዩ ፈጠራዎች ካሉ በተዘጋጀ የውድድር አሠራር መሠረት አሸናፊ ሆነው ለተመረጡ ተማሪዎች በተማሪዎች መንፈስ ላይ መበረታታት ለመፍጠር እንዲችል ውስን የገንዘብ ሽልማት አድርገናል፡፡ ይህም ስህተት ነው አንልም የተጠቀሰውም ዕገዳ ለመንግስት ሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅም በዘፈቀደ አትስጡ ለማለት እንጂ ወጣ ያለ ሥራ የሠሩ አገራዊ ጠቀሜታና ፋይዳ ይፈጥራል በሚል ተስፋ ሰጪ ስራ ለሰሩ ወይም ቢበረታቱ ወደፊት አገራዊ ጠቀሜታ የሚፈጥር ሥራ ይሠራሉ ተብለው ለሚታመንባቸው ተማሪዎች ሽልማት መስጠት በጥንቃቄ ይደረግ ሊባል ይችላል እንጂ ግኝት መሆኑ አግባብነት የለውም ይህን የኦዲት ተቋሙ እኛ ባየንበት ዓይን ቢረዳን በሚል እንገልፃለን ብለዋል፡፡

1.7.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

በስራ አመራሩ ምላሽ ላይ የተሰጠው አስተያየት ማበረታቻው ስህተት ነው አንልም የተጠቀሰውም ዕገዳ ለመንግስት ሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም በዘፈቀደ አትስጡ ለማለት እንጂ ወጣ ያለ ሥራ የሠሩ አገራዊ ጠቀሜታና ፋይዳ ይፈጥራል የሚል ነው፡፡ ሆኖም ዩኒቨርሲቲው በመንግስት ከተፈቀደው ውጪ አስፈላጊ የሆነ ስራ እንደማበረታቻ ሌሎችም አሰራሮች ሲያጋጥመው በዝርዝር ለሚመለከተው አካል በማቅረብ አስፈቅዶ መጠቀም ይገባል፡፡

1.8.1 የግኝቱ፣ ለካዝና መጠባበቂያ የተከፈለ፣

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/03 ባስተላለፈው መመሪያ ላይ ‹‹በስራ አመራር ቦርድ የሚመሩ አንዳንድ የከፍተኛ ትምህርት እና ሌሎች ተቋማት ከመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ውጪ የሰራተኞችን ደመወዝ፣ ጥቅማ ጥቅሞች ለሰራ አመራር ቦርድ እያቀረቡ በማስወሰን ተግባራዊ ማድረጋቸውን ተከትሎ፡፡ጉዳዩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በ4ኛው የምርጫ ዘመን 15ኛው መደበኛ ስብሰባ ላይ ተነስቶ ውይይት ከተደረገበት በኂላ ከጠቅላይ ሚኒስትር ፈቃድ ውጭ ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ /በቦርዱ/ የሰራተኞችን የደመወዝ መጠን ማሻሻል፣ መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና እስከአሁን የተከናወኑም ካሉ ትክክል እንዳልሆነ የተወሰነ መሆኑ እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ ስኬሎች እና ጥቅማጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ ሲል በጥብቅ እንዳሳሰበ መመሪያው ቢያመለክትም፤ የዩኒቨርሲቲው ኤክስኪቲቭ ማኔጂመንት ካውንስል ጥቅምት 19/02/2004 ዓ.ም ለተቋሙ ዋና ገንዘብ ያዥ ብር 300.00፣ እንዲሁም ለረዳት ገንዘብ ያዥ ብር 200.00 የካዝና መጠባበቂያ ክፍያ ከውስጥ ገቢ የሚታሰብ ሆኖ በየወሩ እንዲከፈላቸው ተወስኖ ብር 2,400.00 የተከፈላቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

1.8.2 ስጋት፣

ከመመሪያና ደንብ ውጭ ክፍያ መፈፀም የመንግስት ገንዘብ አላግባብ ወጪ እንዲሆን መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡

1.8.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ከመመሪያ ውጭ አላግባብ የተከፈለው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሰራተኞች ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ዩኒቨርሲቲው መንግስት ባወጣው ደንብና መመሪያ ተከትሎ መስራት ይኖርበታል፡፡

1.8.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በወቅቱ የነበረው ማኔጅመንት የነበረውን አሰራር ተከትሎ ወስኗል፡፡ ይሁንና ሂደቱ ስህተት መሆኑ ስለታመነበት እንዲመለስ እናደርጋለን ብለዋል፡፡

1.9.1 ግኝት፣ የክፍያው መጠን የተፈቀደበት ማስረጃ ያልቀረበ፣

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/03 ባስተላለፈው መመሪያ ላይ በስራ አመራር ቦርድ የሚመሩ አንዳንድ የከፍተኛ ትምህርት እና ሌሎች ተቋማት ከመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ውጪ የሰራተኞችን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞች ለሥራ አመራር ቦርድ እያቀረቡ በማስወሰን ተግባራዊ ማድረጋቸውን በመገንዘብ፣ጉዳዩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በ4ኛው የምርጫ ዘመን 15ኛው መደበኛ ስብሰባ ላይ ተነስቶ ውይይት ከተደረገ በኂላ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ፈቃድ ውጪ ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ /በቦርዱ/ የሰራተኞችን የደመወዝ ስኬል ማሻሻል፣ መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና እስከአሁን የተከናወኑም ካሉ ትክክል እንዳልሆነ የተወሰነ መሆኑ እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ ስኬሎች እና ጥቅማ ጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ ሲል በጥብቅ እንዳሳሰበ ተገልጿል፡፡ በዚህ መሠረት እየተሰራ ያለ መሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- Payment for Adviser ship/student (Net birr 3,500.00)፣
- Payment for External Examiner /Student birr 1,000.00 & birr1,500.00፣
- Payment for Internal Examiner /Student birr 1,000.00 & birr1,500.00 እንዲከፈላቸው በመታዘዙ በቀን 20/10/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0673380 ለ External Examiner ብር 55,500.00 ለ Internal Examiner ብር 108,660.00 በድምሩ ብር 164,160 እና በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 426594፣ 426593 እና 426595 ለExternal Examiner ለ Internal Examiner ድምር ብር 180,000.00 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣
- ለመምህራን ልየታ ቃለ መጠይቅ ለሚያደርጉ የውጪ መምህራን በአንድ ተፈታኝ ብር 200.00 የተጣራ እንዲከፈል በሥራ አመራር ካውንስል ስብሰባ በመወሰን በጀቪ ቁጥር 129305 ብር 49,600.00 ከህግ፣ ደንብና መመሪያ ውጪ መከፈሉ እና ስራውን ለመስራት ውል የገቡበት ከወጪ ማስመስከሪያው ጋር ያልቀረበ መሆኑ፣

በጠቅላላው ብር 393,760.00 የክፍያው መጠን (Rate) በሚመለከተው የመንግሥት አካል የተፈቀደበት ማስረጃ ያልቀረበለት እና ስራው ለመስራት ውል የገቡበት ማስረጃ ከወጪ ማስመስከሪያው ጋር ያልቀረበ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

1.9.2 <u>ስጋት፣</u>

- የወጡ ሕጎች፣ ደንቦችና የአፈፃፀም መመሪያዎች ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- ከሚመለከተው አካል ውጭ የክፍያ መጠን ወስኖ ክፍያ መፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

1.9.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በሚመለከተው ህጋዊ አካል ባልተፈቀደ ክፍያ እና ተመን /ስሌት አለአግባብ እየተከፈለ ያለው ገንዘብ እንዲቆም እና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሥራ ሊያስፈልግ የሚችል ከሆነ ከሚመለከተው አካል በልዩ ሁኔታ ማስፈቀድ ይገባል፡፡

1.9.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ለውስጥ እና ለውጪ ፈታኞች ክፍያ አሠራር በማናቸውም ዩኒቨርሲቲ ያለ ሲሆን ይህም የአከፍፈል ስርዓት ለM.S.C እና ለPHD ትምህርት የግድ ፈታኞች ማምጣት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ይህ ክፍያም ዩኒቨርሲቲዎች እነኝህን ትምህርት የሚያስተምሩ ከሆነ ክፍያው የግድ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ማኔጅመንቱ ወስኖ የተፈፀመ ክፍያ ነው፡፡ ይህን ማቆም የግድ ከሆነ የውጭና የውስጥ ፈታኞች በምን አግባብ ማስተናገድ እንዳለብን የምንቸገር ይሆናል፡፡ ስለዚህ ይህን ክፍያ መፈፀም የግድ ይሆናል የኦዲት ተቋሙም ይህን ሊገነዘብልን ይገባል ፡፡ የኦዲት ግኝት መሆኑን ለሚመለከተው ሚ/ር መስሪያ ቤት መፍትሄ እንዲፈልግ አሳውቀናል በማለት ገልፀዋል፡፡

1.9.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

በስራ አመራር ምላሹ ላይ ይህን ክፍያ መፈፀም የግድ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የኦዲት ግኝት መሆኑን ለሚመለከተው ሚ/ር መስሪያ ቤት መፍትሄ እንዲፈልግ አሳውቀናል በማለት የተገለፀ ስለሆነ ለወደፊት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከተው አካል ጋር በጉዳዩ ላይ በመወያየት መፍትሄ ሊያገኝለት ይገባል፡፡

1.10.1 <u>ግኝት፣ የክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ቁጥር 14 ንዑስ ቁጥር 4 ክፍያ ለሚፈጸምባቸው ክፍያዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት መመሪው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርስቲው፣

- በ24/05/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 463122 በ6256 የሂሳብ መደብ በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደረሰኝ የሌላቸው ልዩ ልዩ ወጪዎች መሰረት የተከፈለ ቢሆንም፣ ደረሰኝ ሊሰጡ የሚችሉ ህጋዊ ድርጅቶችን በመጋበዝ ህጋዊ ደረሰኝ ማግኘት ከሚቻልባቸው ቦታዎች ከተከፈለው ብር 4,467.00 ውስጥ ብር 3,825.00 ደረሰኝ የሌላቸው በሚል የተከፈሉ ሲሆን፣ ለመስክ ጉብኝት የተቆዩባቸው ቦታዎች ወልዲያ፣ ላሊበላ፣ መቀሌ፣ አክሱም እና ጎንደር መሆኑ በ09/05/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 461898 በሂሳብ መደብ 6256 ከተከፈለው ብር 11,429.91 ውስጥ ብር 10,000 እና በ21/02/09 በወጪ ማስመስከሪያ 128460 በሂሳብ መደብ 6232 የተከፈለው ክፍያ የቀረበው ደረሰኝ ለአንድ ጉዞ ብቻ የሚያገለግል ደረሰኝ በመሆኑና ከመኪና አከራይ ድርጅት ያልቀረበ ብር 4,950.00 በድምሩ ብር **18,775.00** ደረሰኝ ያልቀረበለት ተገኝቷል፡፡

1.10.2 <u>ስጋት፣</u>

የመንግስትን ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ ሊዳርግ ይችላል፡፡

1.10.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ህጋዊ የሆኑ የክፍያ ማስረጃዎች መቅረባቸውን በማረጋገጥ ክፍያ መፈፀም ይገባል፡

1.10.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- ክፍያው የተፈጸመው ጎንደር/ፋሲለደስ/፣ ላሊበላ አብያተ ክርስቲያን ፣ አክሱም ሲሆን፣ ተማሪዎቹ ጉብኝት ሲያደርጉ አስጎብኝ የተጠቀሙት አካባቢውን የሚያውቁ ህጋዊ ፈቃድ ያላወጡ ነገር ግን በአስጎብኝነት የሚሰሩ ግለሰቦችን ነው ፡፡ ስራው ስለመሰራቱም አስተባባሪዎች የዲፓርትመንት አምነውበት በቀረበው ደረሰኝ ይወራረድ ብለው በሠጡት ማረጋገጫ የተወራረደ ነው ፡፡
- ለጥበቃ የተከፈለው በተመሳሳይ ተማሪዎቹንና ንብረታቸውን እንዲጠብቁ የአካባቢ ሰዎችን ቀጥረው ያሰሩት ስለሆነ ህጋዊ ደረሰኝ አልቀረበም ፡፡ ይህም በተመሳሳይ ህጋዊ ደረሠኝ የሚሰጡ ስላልሆነ ተማሪዎቹም የሚያድሩት ለውስን ቀን በመሆኑ

ያለጠባቂ ማደርም ስለሌለባቸው በተመሳሳይ በሀላፊዎች ታውቆ እንዲወራረድ የተደረገ ነው ።

- ቀሪው ለፈተና ሂደው ኮንትራት ታክሲ የተጠቀሙት ሲሆን ይሄ መ/ቤቱ በየፈተናው ማዕከል መኪና ስለማይመደብ በመደበኛ ትራንስፖርት ይጠቀሙ ቢባልም የፈተናው ሂደት ሊበላሽ ስለሚችል በማዕከል የተመደቡ አስተባባሪዎች ፈተናውን ከፖሊስ ጣቢያ ወደ ፈተና ማዕከል ከፈተና ማዕከል ወደ ፖሊስ ጣቢያና አውሮፕላን ማረፊያ ድረስ በኮንትራት ታክሲ እንዲጠቀሙ ተፈቅዶላቸው ይህም በልዩ ሁኔታ የፈተና አስተባባሪ ሀላፊ እና ም/ፕሬዚዳንት እንዲያውቁት ተደርጎ የተወራረደ ነው ። ክፍያው ለነዚህ ተግባራት የተፈጸመ ነው። በቀጣይ ግን በህጋዊ አስጎብኝዎች ብቻ እንዲጠቀሙ የጥበቃም የተለየ ችግር ካልገጠመ በስተቀር መንግስታዊ ተቋማት ላይ እንዲያድሩ በማድረግ አሰራሩ በጥብቅ ስርዓት እንዲመራ እናደርጋለን በማለት ገልፀዋል።

1.11.1 <u>ግኝቱ፣ የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ፣</u>

የፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የመደበኛና የካፒታል የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈጸሙ የሚከተሉትን በማሟላት ይሆናል። "ወጪ ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመት (20009) የተያዘ ወይም ወጪውን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪው በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ውስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ዕቅድ ላይ የተካተተ መሆኑ" ሳይረጋገጥ ክፍያ መፈጸም እንደማይገባ መመያው ቢያመለክትም፤ በ22/10/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0673438 ለላየን ሴኩሪቲና የፅዳት አገልግሎት ሀ/የተ/የግ/ማህበር የጥር እና የየካቲት ወር በ2008 ለተሰራ በበጀት ዓመቱ መከፈል ሲገባው፣ በ2009 በጀት ዓመት ብር 715,204.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ተረጋግጧል።

1.11.2 <u>ስጋት፣</u>

- ወጪዎች በጀት ዓመታቸውን ጠብቀው የማይከፈሉ እና የማይመዘገቡ ከሆነ የበጀት ዓመቱን የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታውን ካለማሳየቱም በተጨማሪ የበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድር ይችላል።

1.11.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- የበጀት ዓመቱ ወጪ በበጀት ዓመቱ ክፍያ ተፈፅሞ እንዲመዘገብ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡
- ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ሊፈጸም ይገባል፡፡

1.11.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- በላየን ሴኩሪቲና በዩኒቨርሲቲው መካከል በተፈጠረ ያለመግባባት ክፍያው በጊዜው ለመክፈል ባለመቻሉና የበጀት ዓመቱ በመጠናቀቁ ሲሆን፣ ለወደፊቱ ግን በተሰጠን አስተያየት መሰረት ጥንቃቄ የምናደርግ ይሆናል ብለዋል፡፡

1.12.1 <u>ግኝት፣</u> <u>የሥራ ግብር ሳይቀነስ የተከፈለ፣</u>

- የገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 ምዕራፍ 5 ቁጥር 48/ ንኡስ ቁጥር 1 ሚኒስትሩ ግብርን የሚመለከቱ ስምምነቶችን ከውጭ ሀገር መንግስት ወይም መንግስታት ጋር ሊፈራረም ይችላል ይላል፡፡ በዚህ መሰረት የሚሰራ መሆኑ ኦዲት ሲደረግ፣ በሚኔስተሩ ከግብር ነጻ እንዲሆኑ የተደረገ የውል ስምምነት ሳይቀርብ በዩኒቨርሲቲው የተቀጠሩ የውጭ ሀገር መምህራን የደመወዝና የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ሲፈፀም ብር 2,846,011.34 የሥራ ግብር ተቀናሽ ሳይደረግ ክፍያው የተፈፀመ መሆኑ፣
- የገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 ክፍል ሁለት አንቀጽ 10 (1) ማንኛውም ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ የስራ ግብር ሊከፈልበት እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ፣
    - ከዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ባለሙያዎች በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 660737 እና 660736 በጥር 2009 በተደረገው የደመወዝ ማሻሻያ ብር 1,500.40 እና በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 129287 ብር 999.15 በሚያዝያ 2009 በዩኒቨርሲቲው አዲስ መዋቅር መሰረት የደረጃ እድገት ያገኙ ባለሙያዎች በጊዜው ያልወሰዱት ቀሪ ክፍያ ሲከፍል ተጨማሪውን ብቻ የስራ ግብር እንዲከፈልበት ስለተደረገ በኦዲት ግኝቱ

መሰረት በጥቅምት እና በህዳር /2010 ከተቀነሰባቸው ውጪ ቀሪ በድምሩ ብር 2,499.55 ያልተቀነስ መሆኑ፣

- የሐምሌ 2008 ዓ.ም ከአካዳሚክ ባለሙያዎች ብር 32,626.37 የሚፈለግባቸው የስራ ግብር ያልተቀነስ መሆኑ፣
- ከዩኒቨርሲቲው እና ከውጭ ባለሙያዎች ሊቀነስ የሚገባው የስራ ግብር ብር 73,805.00 የሚፈለግባቸው የስራ ግብር ያልተቀነስ መሆኑን፣

በጠቅላላው ብር 2,954,942.26 የስራ ግብር ሳይቀነስ ክፍያው የተፈፀመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

1.12.2 <u>ስጋት፣</u>

- የወጡ ሕጎች፤ ደንቦችና የአፈፃፀም መመሪያዎች ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- መንግሥት ሊያገኝ የሚገባው ገቢ ላይሰበስብ ይችላል፡፡

1.12.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በአዋጁ መሠረት የሥራ ግብር ሊሰብሰብ ይገባል፡፡ ከባለሙያዎቹ ያልተቀነሰው የሥራ ግብር ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.12.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ከህንድ አገር ተቀጥረው ከመጡ መምህራን ውጭ ያሉ የውጭ ሀገር መምህራን የስራ ግብር መቀነስ ጀምረናል ቀደም ሲል ሊቀነስ ያልቻለው የቅጥር ውላቸው ውስጥ የስራ ግብር ተቀንሶ እንደሚከፈል በግልጽ ባለመቀመጡ ነበር ፡፡
- በአሰራር ስህተት መቀነስ የነበረበት ስራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑን ከኦዲት ግኝቱ ተረድተናል፡፡ በጥቅምት ወር 2010 ደመወዝ ላይ ብር 46,358.44 ተቀናሽ በማድረግ ማስገባት ጀምረናል በህዳር ወር ደመወዝ ይጠናቀቃል በማለት ገልፀዋል፡፡

1.13.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>ከመደበኛ በጀት ለተከታታይ ትምህርት የተከፈለ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት የፋይናንስ ኃላፊነት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ቁጥር 6(ለ) የፋይናንስ

አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ በመመርኮዝ የወጡት መመሪያዎች በመ/ቤቱ ውስጥ በተሟላና ተገቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ይገልፃል:: በተጨማሪም የመንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈፀም ወይም ወጪ ሊደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ብር **1,016,203.37** ከውስጥ ገቢ መክፈል የሚገባውን ከመደበኛ በጀት ለተከታታይ ትምህርት ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

1.13.2 ስጋት፣

- የመንግስትን በጀት ከደንብና መመሪያ ወጪ መጠቀም የመንግስት መመሪያን ከመጣሱም በላይ ለምዝበራና ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡
- ውስን የመንግስት በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ይሆናል ፡፡

1.13.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ከመደበኛ በጀት ለተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም የተከፈለው የሂሳብ ማስተካከያ ሊደረግለት ይገባል፡፡
- ለወደፊቱም ዩኒቨርሲቲው ከተፈቀደለት የሥራ ዘርፍ ውጭ ባልተፈቀደለት በጀት ክፍያ እንዳይፈፅም ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.13.4 የስራአመራሩ ምላሽ፣

ለ2010 በጀት ዓመት ችግሩ እናዳይደገም ይሰራል ብለዋል፡፡

1.14.1 ግኝት፣ ያለሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ የተገኘ፣

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 ተራ ቁጥር 3 መሠረት የሂሳብ እንቅስቃሴዎች በየመደባቸው ተለይተው መመዝገብ እንዳለባቸው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ እንቅስቃሴዎች በመመሪያው መሠረት መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በድምሩ የብር 12,687,847.63 ወጪዎች በተገቢው የሂሳብ መደባቸው ሳይመዘገቡ መገኘታቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

1.14.2 ስጋት፣

የወጪ ሂሳቦች በተገቢው የሂሳብ መደባቸው አለመመዝገባቸው የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛ ከወጪ ቀሪያቸውን እንዳያሳዩ እና የበጀት አጠቃቀሙንም የተዛባ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

1.14.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የተሽከረካሪ አገልግሎት ያገኘነው በተደረገዉ ውል ስምምነት ስለነበር በውል የተፈፀመ ነው በሚል በ6251 ሂሳብ መደብ ክፍያ ሲፈጽም ቆይቷል፡፡ ሆኖም በኪራይ በ6252 መያዝ አለበት ከተባለ ቀን ጀምሮ የታረመና ለወደፊትም በዚሁ መሰረት የምንሰራ ይሆናል በማለት መልስ የተሰጠ ቢሆንም የወጪ ሂሳቦች በተገቢው የሂሳብ መደባቸው አለመመዝገባቸው የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛ ከወጪ ቀሪያቸውን እንዳያሳዩ እና የበጀት አጠቃቀሙንም የተዛባ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት የሰርቪስ መኪና ኪራይ በሂሳብ መደብ 6252 (ኪራይ) መመዝገብ ሲገባው በሂሳብ መደብ 6251(በውል የሚከፈሉ) ተመዝገቦ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በትክክለኛው የሂሳብ መደብ(6252) ቢመዘገብ፣ ለመደቡ ከተደለደለው በጀት በብር 4,777,581.32 ከበጀት በላይ መጠቀማቸውን ያረጋግጣል፡፡

1.14.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

አመዘጋገብ ስህተት የተፈጠረ መሆኑን አይተናል ፡፡ ለወደፊቱ ይህን አይነት ስህተት እንዳይፈጠር አስፈላጊውን ጥንቃቄ እናደርጋለን እናስተካክላለን ብለዋል፡፡

1.15.1 ግኝት፣ የሰርቪስ መኪና ኪራይ አገልግሎት በተመለከተ፣

ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በተፈቀደዉ መሰረት በዩንቨረሰቲው አገልግሎት እየሰጡ ያሉ መምህራን በደብዳቤ ቁጥር 2/4-1182/07 በሚያዚያ 12//2007 ለሌክቸረር 1500፣ ለረዳት ሌክቸረር 1500፣ ለረዳት ፕሮፌሰር 2000፣ ለተባባሪ ፕሮፌሰር 2000 እና ለፕሮፌሰር 2000 በየወሩ እንዲሰጣቸው ተወስኖ ክፍያውን እያገኙ መሆኑ እየታወቀ በተጨማሪ ዩኒቨረስቲው ከንጉሴ ተፈራ የህዝብ ማመላለሻ የግል ትራንስፖረት ማህበር በውል ቁጥር አገ/01/2009 በ01/02/09 በመዋዋል ለዩኒቨርሲቲው ለአስተዳደር ሰራተኞችና ለመምህራን የሰርቪስ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ወደ 7 ያህል አውቶቡሶች ተከራይቶ ወደ አዲሱ ገበያ፣ ካራቆሬ፣ አስኮ፣ ቃሊቲ ማሰልጠኛ፣ ገላን

ኮንዶሚኒየም፣ አያት እና ደብረዘይት ከሰኞ-አርብ ከቤት ወደ ስራ ቦታ ከስራ ቦታ ወደ ቤት መደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል። ይህም የዩንቨርሲቲው መምህራኖች ከተፈቀደላቸው የትራንስፖረት አበል በተጨማሪ የሰርቪስ ትራንስፖረት አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑ፣ የሰርቪስ ትራንስፖረት አገልግሎት ለሚሰጠው ተሽከርካሪ መኪና ኪራይ በመምህራኖቹ ተጠቃሚነት ብዛት ተጨማሪ ወጪ እየተከፈለ መሆኑ፣ በተጨማሪ ከተደረገው የመኪና ኪራይ የውል ስምምነት ውጭ ቅዳሜና እሁድ ፈተና ለሚፈትኑና ለስብሰባ (ለውይይት) በሚል ለመምህራን የትራንስፖርት አበል እየተከፈላቸው በተጨማሪ ሰርቪስ ተመድቦ በሰባቱም አቅጣጫ በድምሩ ብር 2,051,468.00 ለአገልግሎቱ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል። **ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል።**

ቀን	የባንክ ወጪ ማስመ ስከሪያቁጥር	የተመዘገበበት የሂሳብ መደብ	የወጪዉ ምክንያት	የገንዘብ መጠን
4/13/08	0640711	6251	ለመምህራኖች እና ለአስተዳደር ሰራተኞች ወደተለያየ አቅጣጫ ለትራንስፖርት ሰርቪስ ኪራይ የተከፈለ	358,150.00
30/01/09	0830801	6251	>> >> >>	315,172.00
10/12/08	0640361	6251	>> >> >>	300,846.00
30/03/09	0831188	6251	>> >> >>	564,300.00
27/04/09	23585694	6251	>> >> >>	513,000.00
	ድምር			2,051,468.00

1.15.2 <u>ስጋት</u>፣

መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል። በተጨማሪም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።

1.15.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

የዩንቨረስቲው መምህራን የተፈቀደላቸውን የትራንስፖርት አበል ክፍያ ብቻ መውሰድ ካልሆነም የትራንስፖርት ክፍያው ቀርቶ የሰረቪስ አገልግሎቱን ብቻ መጠቀም የሚችሉበት መንገድ በአማራጭ ተቀምጦ የዩንቨረሲቲው መምህራን የትራንስፖርት አበሉን ብቻ የሚወስዱ ከሆነ የትራንስፖረት አገልግሎት የሚሰጠው ተሽከርካሪ ባለው ሰራተኛ ልክ ተከራይቶ ውል ሊገባ ይገባል፡፡

1.15.4 **የስራ አመራር ምላሽ፣**

ዩኒቨርሲቲው በኦዲተሮች እንደተረጋገጠው ለሰርቪስ አገልግሎት የሚሆኑ ከ 7 (ሰባት) ያላነሱ የሶስተኛ ወገን ተሽከርካሪ የምንጠቀም ሲሆን፣ ሰርቪስ እንዲሰጡልን የተከራየነው ለአሰተዳደር ሰራተኛው እንጂ የትራንስፖርት አበል ለምንከፍላቸው መምህራን አይደለም፡፡ ነግር ግን መምህራኖች የዩኒቨርሲቲውን መኪና ሲያገኙ ተሳፍረው የሚመጡበት ሁኔታ እንዳለ ይታወቃል፡፡ ለወደፊቱ በተሰጠው አስተያየት መሰረት በተቻለ መጠን ለአስተዳደር ሰራተኞች በሚመጥን መልኩ የሰርቪስ ኪራያችንን ለማሻሻል የምንሞክርና በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት የምንፈጽመው ይሆናል በማለት ገልፀዋል፡፡

1.15.5 **የኦዲተሩ አስተያየት፣**

በስራ አመራሩ ምላሽ ላይ ሰርቪስ እንዲሰጡልን የተከራየነው ለአሰተዳደር ሰራተኛው እንጂ የትራንስፖርት አበል ለምንከፍላቸው መምህራን አይደለም ተብሎ መልስ የተሰጠ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በውል ቁጥር አገ/01/2009 ቀን 01/02/2009 የውሉ መሰረት በሚለው ርዕስ ስር የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩንቨርስቲ ለመምህራን እና ሰራተኞች መደበኛ ትራንፖርት አገልግሎት ለመስጠት በሚል ከንጉሤ ተፈራ የህዝብ ማመላለሻ የግል የትራንስፖርት ማህበር ጋር የተዋዋሉ ለመሆኑ ውሉ በማስረጃነት ከኦዲት ማስታሻው ጋር ተያይዟል፡፡ ስለሆነም ለወደፊት በአሰተዳደር ሰራተኛው ቁጥር ልክ ብቻ የስርቪስ መኪናውን መከራየት ይገባል፡፡

1.16.1 **ግኝት፣ለህንፃ ተቋራጭ የተከፈለ የመያዣ ሂሳብ በተመለከተ፣**

የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 ተራ ቁ 7/3 መሠረት የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች በዕቅድ ሳይካተት ወይም ከሚኒስቴሩ

የክፍያ ጣሪያ ያልተጠየቀለት ድንገተኛ ወጪ ሲያጋጥም የክፍያ ማስተላለፊያ ሂሳባቸው ውስጥ በቂ ጣሪያ አለመኖሩን በማረጋገጥ ተጨማሪ የክፍያ ጣሪያ እንዲሰጣቸው በመ/ቤቱ ኃላፊ ወይም እርሱ በሚወክለው ሠራተኛ ጥያቄው ለሚኒስቴሩ መቅረብ እንደሚገባው ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ በዩኒቨርሲቲው በዕቅድ ያልተያዘ እና በጀት ያልተፈቀደለት የኮንትራት መያዣዎች ሂሳብ በድምሩ ብር 1,212,589.7 በሂሳብ መደብ 5061 እና 6323 በወጪ ተይዞ ለተለያዩ የህንፃ ተቋራጮች ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ **ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡**

ተ.ቁ	ቀን	ገንዘቡ የተከፈለ/ድርጅት	የቫውቸር ቁጥር	ሂሳብ መደብ	የገንዘብ መጣን
1	21/04/09	ሙሉጌታ አበበ ህ/ስ/ተቋራጭ	426668	5061	724,394.48
2	21/04/09	ሙሉጌታ አበበ ህ/ስ/ተቋራጭ	426670	5061	235,389.49
3	20/04/09	መሰረት አዲሱ ህ/ስ/ተቋራጭ	426664	5061	17,315.76
4	02/03/09	ኤም.ኤስ.ኤስ ስፖርት ሰርቪስ ኃላ.የተ.የግ.ማ	0640300	5061	44,995.00
5	02/08/09	ንጉሱ ከለሎም ህንፃ ሥራ ተቋራጭ	0671679	6323	55,966.60
6	02/08/09	ንጉሱ ከለሎም ህንፃ ሥራ ተቋራጭ	0671680	6323	57,372.85
7	1/9/09	ንጉሱ ከለሎም ህንፃ ሥራ ተቋራጭ	0671681	6323	77,155.52
		ድምር			1,212,589.70

1.16.2 ስጋት፣

- የበጀት ዓመቱን የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛነት ላያሳይ ይችላል፡፡
- በዕቅድ ያልተያዙ ክፍያዎች የዩኒቨርሲቲውን የበጀት አጠቃቀም የተዛባ እንዲሆን ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

- ዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ላያውል ይችላል፡፡

1.16.3 **<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>**

- ክፍያው የመንግስትን የክፍያ መመሪያ ያልተከተለ በመሆኑ በሥራ አመራሩ ክትትል ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል:: ለወደፊቱም በጀት ያልተፈቀደላቸው ክፍያዎች እንዳይፈፀሙ ተገቢው ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡
- ለማይገባቸው ኮንተራክተሮች ክፍያ ተፈፅሞ ሊሆን ስለሚችል በውስጥ ኦዲተር ተጣርቶ የተከፈሉት ዕዳዎች በእርግጥም ሊከፈሉ የሚገባ ስለመሆኑ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

1.16.4 **<u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>**

በስህተት ለተመዘገበው በጀት ኮድ ማስተካከያ ያደረግን መሆኑን እየገለፅን ማስተካከያ የተሰራበት **ጄቪ ቁጥር 129082 በአባሪ 5 ተያይዟል** በማለት ገልፀዋል፡፡

1.16.5 **<u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>**

በስራ አመራሩ ምላሽ ላይ በስህተት በ6323 ለተመዘገበው በጀት ኮድ ማስተካከያ የተሰራለት መሆኑ ተገልጿል፡፡ ሆኖም ይህ ብቻ ሳይሆን በዩኒቨርሲቲው በዕቅድ ያልተያዘ እና በጀት ያልተፈቀደለት የኮንትራት መያዣዎች ሂሳብ ተከፍሎ በመገኘቱ የአከፋፈል ሁኔታው ላይ ተገቢ የሆነ የማጣራት ስራ በውስጥ ኦዲተር ተጣርቶ የተከፈሉት ዕዳዎች በእርግጥም ሊከፈሉ የሚገባ ስለመሆኑ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

1.17.1 **ግኝት፣ <u>የህንጻ ግንባታን በተመለከተ(አማካሪ ድርጅት)፣</u>**

ሰኔ /2002 በወጣው የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ክፍል 7 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 5 (ሀ) የመንግሥት መ/ቤት ለግንባታ ዘርፍ ክፍያ የሚፈፀመው የሥራውን ደረጃ ተከትሎ ከአማካሪ መሐንዲስ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት መነሻነት ብቻ መሆን እንዳለበት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በመመሪያው መሠረት ክፍያ መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በድምሩ ብር 27,592,730.23 በዩኒቨርስቲው የግንባታ ጽ/ቤት መሀንዲስ እና በህ/ሥ/ተቋራጮች በተዘጋጀ የክፍያ ሰርተፍኬት እና በሥራ አመራሩ ፀድቆ እንዲከፈል መደረጉ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

1.17.2 ስጋት፣

- መንግሥት ያወጣቸዉ አዋጅ፤ ደንቦች እና የአፈፃፀም መመሪያዎች ሥራ ላይ እንዳይውሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- የመንግስት እና የህዝብ ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ማረጋገጥ አያስችልም፡፡

1.17.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- በመንግሥት በወጡ አዋጅ፣ ደንቦች እና የአፈፃፀም መመሪያዎች መሠረት ክፍያዎች ተረጋግጠው መከፈል ይኖርባቸዋል፡፡
- የመንግስት እና የህዝብ ገንዘብ ለታለመለት ዓለማ እንዲውል የውስጥ ቁጥጥር ማጠናከር ይገባል፡፡
- የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ይህንን የማማከር አገልግሎት ህጋዊ ፈቃድ ያልተሰጠው በመሆኑ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ በፍጥነት ሊወሰድ ይገባል፡፡

1.17.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፤

- 2006 ዓ.ም በተሸሻለው የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጄንሲ ባዘጋጀዉ መደበኛ የጨረታ ስነድ ዉስጥ እንደተገለፀዉ አማካሪ መሀንዲን ማለት በልዩ የውል ሁኔታዎች ዉስጥ የተሰየመ ወይም በግዢ ፈፃሚ አካሉ (በመንግስት አካሉ) የግንባታ ሥራዎችን አንዲቆጣጠርና እንዲከታተል በሥራ ላይ የዋሉ ቁሶችን የትግበራ ጥረት እንዲፈትሽ እንዲመረመር በጽሁፍ የተመደበ ግለሰብ ወይም የግለሰቡ ወኪል ማለት ነዉ ብሎ በገለጸዉ መሰረት የተቋሙ ማኔጀመንት በቃለጉባኤ ቁጥር 34/2007 ባሳለፈው ውሳኔ ከሲቨል ምህንድስና ኮሌጅ በተውጣጡ እና በዘርፉ ሰፊ ልምድ ባላቸዉ መምህራን የግንባታ ስራዉን ክትትል ሲያደርጉ እና ከላይ የተጠቀሰዉን የገንዘብ መጠን ተቋራጩ ላከናወነዉ ስራ የተጠየቀዉ እና አማካሪ መሐንዲሱ አረጋግጦ ያቀረበዉ በመሆኑ ክፍያዉ እንዲፈጸም የውሳኔ ሀሳብ የቀረበ ሲሆን የፌዴራል ዋና ኦዲተር አሰራሩ ማስተካከያ መደረግ እንደሚገባዉ ባሳወቀን መሰረት ከ22/09/09 ጀምሮ አሰራሩ እንዲቆም ተደርጓል በማለት ገልፀዋል፡፡
- እንደሚታወቀዉ ዩኒቨርስቲዎች የግንባታ ስራውን ከትምህርት ሚኒስቴር ተረክበዉ ግንባታዉን ስራዉን በባለቤትነትና በሀላፊነት ለማስፈጸም የአካዳሚክና

የድጋፋ ሰጭ ሃይላቼዉን አደራጅተዉና የሰዉ ሀይል አሟልተዉ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ተቋቁመዉ ስራ ጀምረዋል፡፡ ይሁን እንጅ የግንባታ ጽ/ቤቱ የሰዉ ሀይል ስላልነበረዉ የተቋሙ ማኔጂመንት ባሳለፈዉ ዉሳኔ መሰረት ከሲቪል ምህንድስና ኮሌጅ ሰፊ ልምድ ያላቸዉ መምህራንን በመምረጥ እና ዉል በመዋዋል የግንባታ ጸ/ቤቱ የምክር አግልግሎት በመስጠት ሲያግዙ ቆይተዋል፡፡ እነዚሁ መምህራን ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ጋር ተመሳሳይ ትላልቅ የመንገድ ፕሮጀክቶችን የማማከር ልምድ ያላቸዉ ናቸው ብለዋል፡፡

1.18.1 ግኝት፣ በፕሮጀክት ጽ/ቤት የሚከናወኑ ግንባታዎች፣

በዩኒቨርስቲው የሰው ኃይል የሚከናወኑ የግንባታ ሥራዎች አፈጻጸም እንዲሁም ለግንባታው የወጣውን ወጪ ዩኒቨርስቲው ለተጠቀመበት አገልግሎት የዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ከፍተኛ ዋጋ በሚጠይቁና ውስብስብ ወይም ቴክኒካል የሆኑሥራዎች በሙያው ፍቃድና በቂ እውቀት ያላቸው የውጭ አማካሪዎች በመቅጠር ማሰራት እንደሚገባ በመንግስት በወጣው የግዥ መመሪያ ላይ የተመለከተ ቢሆንም፣ የዩኒቨርስቲው ኢንጅነሪንግና የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከሚመለከተው ክፍል የተሰጠ አማካሪ መሃንዲስ ለመሆን የሚያስችል የስራ ፍቃድ ሳይኖረው በስራ ተቋራጮች መከናወን የሚገባቸው ብር 154,766.67 ዋጋ ያላቸው ፕሮጀክቶች የማማከር፣ ዲዛይን የመስራት፣ ጨረታ የመገምገም ሥራዎች የሚያከናውን መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝር ሁኔታው ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ተራ ቁጥ	ወጪ የሆነበት ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የገንዘብ መጠን
1	24/04/09	426672	6251	39,300.00
2	6/04/09	426663	6251	99,000.00
3	15/03/09	426655	6251	12,000.00
4	21/02/09	0640289	6251	4,466.67
	ድምር			154,766.67

1.18.2 ስጋት፣

ተከታታይነት ያላቸው ሥራዎች በግንባታ ጽ/ቤቱ መከናወን ለክትትልና ለቁጥጥር አመቺ ካለመሆኑም በተጨማሪ መንግሥት ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ ያደረገባቸው የግንባታ ሥራዎች ጥራትና ደረጃ ተጠብቆ ባለመሠራት መንግሥትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡ ለሚደርስ የግባታ ሥራ ግድፈት ተጠያቂነት እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

1.18.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የግንባታ ሥራዎቹን የማማከር አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የሙያ ፍቃድ ባላቸው ባለሙያዎች ሊከናወኑ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት የሥራ አመራሩ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.18.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የተሰጠውን አስተያየት ተቀብለን ለወደፊት የምንተገብር ይሆናል ብለዋል፡፡

1.19.1 ግኝት፣ የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ፣

የፌዴራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል አራት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 የመንግስት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ፣ ቅባት፣ ዘይት አጠቃቀም እና ቁጥጥር በሚለው ስር ‹‹ለበላይ ኃላፊዎች እና ለኃላፊዎች ከሚመደቡ ተሽከርካሪዎች በስተቀር እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የሚጠቀመው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር መጠን ጋር እየተመዘገበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ መቅረብ እንደሚኖርበት›› መመሪያው ቢያመለክትም፣ በዩኒቨርሲቲ ስር የሚገኙት ተሽከርካሪዎች በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተጠቀሙት የነዳጅ መጠንና ከሸፈኑት የኪ/ሜትር ርቀት በየወሩ ምዝገባ እየተከናወነ ተገቢው ሪፖርት ከጠቅላላ አገልግሎት እንዲቀርብ ተጠይቆ በቀረበው ማስረጃ መሰረት፤ በጠቅላላው ከሾፌሮች 13,095.27 ሊትር ነዳጅ በጉድለት የሚፈለግ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

1.19.2 ስጋት፣

በደንቡ መስረት በተቀመጠው የነዳጅ ፍጆታ መሰረት ተግባራዊ አለማድረግ አላግባብ የመንግስትን ገንዘብ ወጪ የሚያስደርግና ለግለሰቦች ጥቅም ሊውል የሚችል ይሆናል፡፡

1.19.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በበጀት ዓመቱ ለተቋሙ ተሽከርካሪዎች ከተቀዳው ነዳጅ ውስጥ በጉድለት ከአሽከርካሪዎቹ የሚፈለገው ነዳጅ ተመላሽ እንዲደረግ፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት የመንግስት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ፣ ቅባትና ዘይት አጠቃቀም እና ቁጥጥር በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆን የተቋሙ የስራ አመራር ተግባራዊነቱን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

1.19.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በከተማ አንበሳ አውቶቡስ ድርጅት በኩል ኖርማላይዜሽን እያሰራን ስለሆነ በሚሰጠን ውጤት መሰረት በውስጥ ኦዲት አሰርተን ውጤቱን የምንገልፅ ይሆናል ብለዋል፡፡

2. <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

2.1.1 <u>ግኝት</u>፣<u>በወቅቱ ያልተሰበሰበ ሂሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ የሚወራረድ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከሚታየው ውስጥ በድምሩ ብር 5,809,058.61 እስከ 2009 በጀት ዓመት መጨረሻ መወራረድ ሲገባው፣ ያልተወራረደ መሆኑንና፣

- በሂሳብ መደብ 4201 /ልዩ ልዩ ቅድሚያ ክፍያ/ ብር 3,181,551.65 ከወር- 3 ዓመት ለውሎ አበል ቅድሚያ የተከፈለ፣
- በሂሳብ መደብ 4211 ብር 2,627,506.96 በተለለያዩ ጊዜ ለግዥ ቅድሚያ ክፍያ ተከፍሎ ከ 4 ዓመት በላይ ያልተወራረደ መሆኑ፣

በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

2.1.2 <u>ስጋት፣</u>

- የመንግስትን ገንዘብ በወቅቱ አለመሰብሰብ ለገንዘብ ጥፋትና ብክነት መንስዔ ሊሆን ይችላል፡፡
- በቅድሚያ የተከፈለው ገንዘብ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲወራረድ ቁጥጥር ካልተደረገ ለውዝፍ ሰነድ ክምችት መንስዔ ይሆናል፡፡
- ተሰብስቦ ሥራ ላይ ሊውል የሚችል ውስን ሀብት /ገንዘብ/ ያለሥራ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡

2.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በውዝፍ የሚገኘው ተሰብሳቢ ሂሳብ በአፋጣኝ እንዲወራረድ፤ ለወደፊቱም የቅድሚያ ክፍያዎች በደንቡ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲወራረዱ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ፤ የእርምት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

2.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በ 4201 በተሰብሣቢ ከተያዘው 3,181,551.65፡-

- ለኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ስፖንሰርነት ለሚማሩ ተማሪዎች ለምረቃ ጽሁፍ ዝግጅታቸው በቅድሚያ የሚሠጣቸው እና ሲመረቁ የሚያወራርዱት ብር 1,980,000.00፣ ማስረጃው በአባሪ 6 ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡
- መስክ ለወጡ ሠራተኞች እና ለውስጥ ተመራማሪዎች ስራቸውን አጠናቀው እንደመጡ የሚያወራርዱት ብር 1,201,551,65 የነበረ ሲሆን አሁን ተወራርዷል ብለዋል፣

2.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት፡፡

- በስራ አመራር ምላሹ ላይ ተማሪዎች ለምረቃ ጽሁፍ ዝግጅታቸው በቅድሚያ የሚሠጣቸው እና ሲመረቁ የሚያወራርዱት ብር 1,980,000.00፣ ማስረጃው በአባሪ 6 ላይ ይገኛል የተባለው እና ተመራማሪዎች ስራቸውን አጠናቀው እንደመጡ የሚያወራርዱት ብር 1,201,551,65 የነበረ ሲሆን አሁን ተወራርዷል የተባለው የተወራረደበት ማስረጃ ለኦዲት ያልቀረበ በመሆኑ በተሰብሳቢነት እንደተያዘ ነው፡፡

2.2.1 ግኝት፣ ሚዛኑን ያልጠበቀ የተሰብሳቢ መክፍቻ ሂሳብ፣

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/6 ፊደል መ መሠረት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የጊዜያዊ ሂሳቦች መዝጊያ ምዝገባ ተከናውኖ የዘመኑን ሂሳብ በመዝጋት ቋሚ ሂሳቦች ለቀጣዩ በጀት ዓመት መተላለፍ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የነበሩ ቋሚ ሂሳቦች በትክክለኛው የሂሳብ ሚዛን /Normal balance side/ ወደ ቀጣዩ በጀት ዓመት መተላለፋቸው ኦዲት ሲደረግ፡

- በመክፈቻ ሂሳብ /Opening balance/ በተሰብሳቢ ሂሳብ በተለያዩ ተቀጽላ ቋት /ሌጀሮች/ ብር 11,129,206.79 አግባብ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን ክሬዲት ሂሳቡ የሚታይ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

2.2.2 <u>ስጋት፣</u>

በሂሳብ መዝጊያና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት የሂሳብ ቋቶች ትክክለኛውንና ተገቢውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው ካልተረጋገጠ የሂሳብ ሪፖርቶች የተቋሙን የፋይናንስ እንቅስቃሴ በትክክል ላያሳዩ ይችላሉ፡፡

2.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በሂሳብ መዝጊያና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት የሂሳብ ሌጀሮች ተገቢውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው ሳይረጋገጥ ሪፖርት እንዳይደረግ ተገቢውን ጥንቃቄ መውሰድ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ለሂሳቡ ተገቢውን ማስተካከያ ሊደረግበት ይገባል፡፡

2.2.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ከ2004 እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ በተለያየ ምክንያት የሂሳብ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ሂሳቦች እንዳሉ አይተናል፡፡ በ2010 ዓ.ም ሙሉ ለሙሉ የሚስተካከል ይሆናል በማለት ገልፀዋል፡፡

2.3.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ከውሎ አበል በተጨማሪ የአልጋ ሂሳብ በቅድሚያ የተከፈለ፣</u>

ለመንግስት ሰራተኞች ወደ መስክ በሚሄዱበት ጊዜ የሚሰጣቸው ቅድመ ክፍያ የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል መመሪያ ሰኔ 2004 ዓ.ም ክፍል 2 አንቀጽ 4 የውሎ አበል ተመንና አከፋፈል መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ዩኒቨርስቲው ለሚገቡ ተማሪዎች ፈተና ለመፈተን እንዲቻል ቅድመ ሁኔታዎችን ለማጥናትና ለማስተካከል የተመደቡ ባለሙያዎች ለስራ የሚሆን የ14 ቀን የውሎ አበል እና ለእያንዳንዳቸው በሚያቀርቡት ህጋዊ ደረሰኝ የሚወራረድ የአምስት ቀን የአልጋ ኪራይ (በቀን እስከ ብር 500 የሚደርስ) ብር 2,500.00 እንዲሰጣቸው በመደረጉ የአልጋ ኪራይ ያለ አግባብ ብር 40,000.00 የተከፈለ እና በበጀት ዓመቱ ያልተወራረደ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

2.3.2 <u>ስጋት፣</u>

- በመመሪያ መሰረት ክፍያ ካልተፈፀመ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡
- ከመመሪያ ውጭ ክፍያ መፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

2.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ ክፍያ መፈፀም ይገባል፡፡
- የቀን ውሎ አበል የሚከፈለው የቁርስ፣ የምሣ፣ የዕራት እና የአልጋ ታሳቢ ተደርጎ ስለሆነ ያለአግባብ የተፈፀመው የአልጋ ኪራይ ክፍያዎች ተመላሽ ሊደረጉ እና ለወደፊትም ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ሂሳቡ በሚወራረድበት ጊዜ ለአበል የተወሰደው በቆዩበት ቀን ብቻ መሰራት ይኖርበታል፡፡

2.3.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ክፍያው የተፈፀመው የአዲስ ተማሪዎችን መግቢያ ፈተና ለማስፈፀም ሲሆን ይህም ስራ በሳይንስና ቴክኖሎጂ አስተባባሪነት የሚመራና አጠቃላይ ለሥራው የሚያስፈልገው ወጪና አፈጻጸም ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በተላከው መሠረት የተፈፀመ ነው ክፍያው ግን አዲስ መመሪያ እስኪሰጠን ድረስ እንዲቆም ተደርጓል ብለዋል፡፡

3. የተከፋይ ሂሳብ፣

3.1.1 ግኝት፣ በወቅቱ ያልተከፈለ ሂሳብ፣

የዩኒቨርሲቲው ተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ የሚከፈል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የሚታይ ተከፋይ ሂሳብ በድምሩ ብር 1,874,046.93 እስከ 2009 በጀት ዓመት መጨረሻ መከፈል ሲገባው፣

- በ5028 /በመንግስት መ/ቤቶች መካከል ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች/ የሂሳብ መደብ ብር 2,204,709.86 ከነበረው ውስጥ ያልተከፈለ ቀሪ ብር 1,874,046.93 ከወር-3 ዓመት ሳይከፈል የቆየ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

3.1.2 ስጋት፣

ተከፋይ ሂሳቦችን ለባለቤቶቹ በወቅቱ አለመክፈል ለገንዘብ መጥፋት መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡

3.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ተከፋይ ሂሳቦችን ለባለቤቶቹ በወቅቱ መክፈል፣ የማይከፈሉ ከሆነም በፋይናንስ ህጉ መሰረት ተገቢው ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

3.1.4 የስራ አመራሩ ምለሽ፣

በ5028 ሂሳብ መደብ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃ/ሠ/ማ ብር 330,662.93 ተከፍሏል፡፡ ማስረጃው በአባሪ 9.3 ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡

3.2.1 ግኝት፣ሚዛኑን ያልጠበቀ የተከፋይ መክፍቻ ሂሳብ፣

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/6 ፊደል መ መሠረት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የጊዜያዊ ሂሳቦች መዝጊያ ምዝገባ ተከናውኖ የዘመኑን ሂሳብ በመዝጋት ቋሚ ሂሳቦች ለቀጣዩ በጀት ዓመት መተላለፍ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የነበሩ ቋሚ ሂሳቦች በትክክለኛው የሂሳብ ሚዛን /Normal balance side/ ወደ ቀጣዩ በጀት ዓመት መተላለፋቸው ኦዲት ሲደረግ፡

- በመክፈቻ ሂሳብ /Opening balance/ በተከፋይ ሂሳብ በተለያዩ ተቀጽላ ቋት /ሌጀሮች/ ብር 2,379,927.89 አግባብ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን በዴቢት የሚታይ መሆኑ፡፡

3.2.2 ስጋት፣

በሂሳብ መዝጊያና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት የሂሳብ ቋቶች ትክክለኛውንና ተገቢውን የሂሳብሚዛን ማሳየታቸው ካልተረጋገጠ የሂሳብ ሪፖርቶች የተቋሙን የፋይናንስ እንቅስቃሴ በትክክል ላያሳዩ ይችላሉ፡፡

3.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በሂሳብ መዝጊያና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት የሂሳብ ቋቶች ተገቢውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው ሳይረጋገጥ ሪፖርት እንዳይደረግ ተገቢውን ጥንቃቄ መውሰድ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ለሂሳቡ ተገቢውን ማስተካከያ ሊደረግበት ይገባል፡፡

3.2.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

2004 እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ በተለያየ ምክንያት የሂሳብ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ሂሳቦች እንዳሉ አይተናል፡፡ በ2010 ዓ.ም ሙሉ ለሙሉ የሚስተካከል ይሆናል ብለዋል፡፡

4. **በጀት፣**

4.1 **ግኝት፣ያልተሰራበትና ከበጀት በላይ የወጣ በጀት፣**

ለዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የተፈቀደው በጀት በአግባቡ ስራ ላይ የዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ለመደበኛ (1800) ወጪ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ መደቦቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር **100,123,961.82** ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤
- ከውስጥ ገቢ (1900) ወጪ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ መደቦቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር **14,553,637.00** ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤
- ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ መደቦቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር **258,459,726.48** ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣

ተረጋግጧል፡፡

4.2 **ስጋት፣**

ዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የታወጀለትን በጀት አለመጠቀሙ ሊደርስበት ካቀደው ግብ እንዳይደርስ ከማድረጉም በላይ የሀገሪቱንም ውስን ሃብት ያለጥቅም እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡

4.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

- ዩኒቨርሲቲው በበጀት አጠቃቀሙ ላይ የተመደበለትን በጀት በአግባቡ መጠቀም ይኖርበታል፡፡ ዕቅድና ክንውኑም የተጣጣመ ሊሆን ይገባል፡፡

4.4 **የስራ አመራሩ ምላሽ፣**

የስራ አመራሩ ተቀብሎታል፡፡

5. **ንብረት፣**

5.1.1 **ግኝት፣የንብረት አያያዝና አጠባበቅ በተመለከተ፣**

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 5 የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ

ማስወገድ እንዳለባቸው ያዛል፡፡ በዚህ መሰረት የዩኒቨርስቲውን የንብረት አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና አጠባበቅ በተመለከተ በተደረገው ኦዲት፣

- በተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ዕቃዎችን መቆጣጠሪያ ካርድ (UC) ለተጠቃሚዎች ያልተሰጠ መሆኑ፣
- ለቋሚ ዕቃዎቹ መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው በስጦታ የተቀበላቸው መኪናዎች ሠ.ቁ 4-21229፣ 4-15080 በባለሙያ ዋጋቸው ያልተተመነ መሆኑ፣
- የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ የተደረገው በዕቃ መጋዘን (ስቶር) ውስጥ ያሉትን ብቻ እንጂ በየቢሮው ያሉ ቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ ያልተደረገላቸው መሆኑ፣
- በተማሪዎች ምግብ ቤት ንብረት ክፍል ውስጥ አገልግሎታቸው ያለፈባቸው ብዛታቸው 916 ጣሳ የሚሆኑ ማርማራታ መኖራቸው፣ በተጨማሪም የተበላሹ የምግብ አቅርቦቶች /ብጣሪዎች/ መኖራቸው፣
- በቋሚ ዕቃዎች ግምጃ ቤት የቋሚ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እና የንብረት ወጪ ደረሰኝ በአንድ ሰው የሚዘጋጅ መሆኑ፣
- በተማሪዎች ምግብ ማብሰያ ክፍል ውስጥ ባለ አራት የምግብ ማብሰያዎች (ኩኪንግ ማሽን ወይም እስቶፍ) ብዛት 21፣ የዳቦ ማቡኪያ ማሽን 2 ጥገና ሳይደረግላቸው ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆናቸው፣
- የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድሃኒቶች ከ2 ዓመት በላይ ሳይወገዱ በመፀዳጃ ቤት ውስጥ እንዲቀመጡ መደረጉን፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ወደ 75 የሚሆኑ ዲስክ ቶፕ ኮምፒተሮች ሳይወገዱ ከሁለት ዓመት በላይ በቋሚ ንብረት ክፍል ውስጥ ተቀምጠዉ መገኘታቸው፣

በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

5.1.2 <u>ስጋት፣</u>

- ተገቢው የንብረት አያያዝ ሥርዓት ተግባራዊ ባለመደረጉ በመንግሥት ውስን ሀብት የተገዙት ንብረቶች ለብክነትና ለምዝበራ ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡
- የተበላሹ ምግቦች በሰዓቱ ባለመወገዳቸው በተማሪዎች ጤና ላይ ጉዳት ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡

- ንብራቶቹ ባለመቆጠራቸው ምክንያት ያሉና የሌሉ ንብረቶች ላይታወቁ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም መንግስትንም ላልተፈለገ ወጪ ይዳርጋል፡፡

5.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

- ንብረቶች በØÁ‰L S”ÓYƒ ”w[ƒ ›e}ÇÅ` SS]Á q$_R 9¼2003 መሰረት ሊያዙና ሊጠበቁ ይገባል፡፡
- የቋሚ ንብረት የገቢና ወጪ ደረሰኝን በተመለከተ ዩንቨርስቲው በቂ የሰው ኃይል በመመደብ በተለያዩ ባለሙያ እንዲሰራ እያደረገ ይገኛል በማለት ምላሽ የተሰጠ ቢሆንም፣ በኦዲቱ ወቅት ይህ ሆኖ ስላልተገኘ ንብረት ክፍልን በበቂ የሰው ኃይል በማደራጀት ተነጣጥለው መሰራት የሚገባቸው ስራዎች በአንድ ሰው እንዳይሰሩ ለማድረግ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡
- በንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኙ መወገድ ያለባቸው ንብረቶች የግዥና ንብረት አስወጋጅ አገልግሎት ጋር በመነጋገር የሚወገዱበትን ስርዓት ማመቻቸት እና አገልግሎት የማይሰጡ የተለያዩ የምግብ ቤትና የቢሮ ዕቃዎች በባለሙያ እንዲታዩ በማድረግ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉትን በአገልግሎት ላይ እንዲውሉ፤ የማያገለግሉትንም በመለየት በስጦታ እና በሽያጭ የሚወገዱበትን ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል፡፡
- እንዲሁም የመድሃኒት ንብረት ክፍል ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግና በክሊኒክ ውስጥ የሚገኙትን የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈ መድሀኒቶች ከሚመለከተው የስራ ክፍል ጋር በመነጋገር የሚወገዱበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖረበታል፡፡

በአጠቃላይ በዩኒቨርሲቲው የንብረት አያያዝ፣ አጠባበቅ፣ አመዘጋገብ እና አወጋገድ ስርዐት በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ የሚደረግበት አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡

5.1.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

- በተሰጠው አስተያየት መሰረት የምናስተካክል ይሆናል ፡፡ ነገር ግን ሁለት የዳቦ ማቡኪና መጋጋሪያ ማሽን ተሸጠዋል፡፡ ሌሎችንም ለማስወገድ የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ ተዋቅሮ በመስራት ላይ ነን ፡፡ ማስረጃው በአባሪ 11 ላይ ይገኛል በማለት ገልፀዋል፡፡
-

5.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

በስራአመራሩ ምላሽ ላይ ሁለት የዳቦ ማቡኪና መጋጋሪያ ማሽን ተሸጠዋል የተባለው የቀረበው ማስረጃ ሁለት የዳቦ መጋጋሪያ ብቻ የተሸጠ መሆኑን ስለሚገልፅ ለወደፊት ሁለቱን የዳቦ ማቡኪያ በመሸጥ ማስወገድ ይገባል፡፡

5.2.1 ግኝት፣ የተሽከርካሪዎች መለዋወጫ ዕቃ አጠቃቀምና ቁጥጥር፣

የፌዴራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 አንቀጽ 10/1 ማንኛውም የመስሪያ ቤቱ አሽከርካሪ ወይም በራሱ እንዲያሽከረክር የተፈቀደለት ኃላፊ ያረጀ ጎማና ቸርኬን ጨምሮ የመለዋወጫ ዕቃ በአዲስ እንዲተካለት ሲጠይቅና የጥያቄው ትክክለኛነት አግባብ ባለው ባለሙያ ሲረጋገጥ በአዲስ እንዲተካለት የሚደረግ ሲሆን፣ የተቀየረው መለዋወጫ ዕቃ ወደ ዕቃ ግምጃ ቤት ተመላሽ ተደርጎ ይቀመጣል፡፡በዚህም መሰረት ወደ ዕቃ ግምጃ ቤት ተመላሽ የሚደረገው የመለዋወጫ ዕቃ መለያ ቁጥር (serial number) ከዕቃ ግምጃ ቤት በሚላከው መረጃ መሰረት ቀደም ሲል ከተመዘገበበት መዝገብ ጋር ተመሳክሮ ሲረጋገጥ ያገለገሉ ዕቃዎች ወደ የሚከማቹበት ቦታ እንዲላክ ይደረጋል፡፡ የመለዋወጫ ዕቃው መለያ ቁጥርም በተሽከርካሪው የግል ማህደር ውስጥ ተመዝግቦ እንዲቀመጥ መደረግ አለበት፤ ቢልም ገቢ የሚደረገው /የተቀየረው/ ንብረት ቀደም ሲል በንብረት ክፍል ከተመዘገበው መለያ ቁጥር ጋር የማይመሳከር መሆኑና አዲስ የተለወጠው መለያ ቁጥር የማይመዘገብ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

5.2.2 ስጋት፣

- የተቀየረው ዕቃ ያለቀ ወይም የተበላሸ መሆኑን ማወቅ አያስችልም፡፡
- ተቀይሮ ገቢ የተደረገው ዕቃ በሌላ ተመሳሳይ ዕቃ ተለውጦ ሊሆን ይችላል፡፡

5.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ወደ ዕቃ ግምጃ ቤት ተመላሽ የሚደረገው የመለዋወጫ ዕቃ መለያ ቁጥር (serial number) ከዕቃ ግምጃ ቤት በሚላከው መረጃ መሰረት ቀደም ሲል ከተመዘገበበት መዝገብ ጋር ተመሳክሮ ሲረጋገጥ ብቻ መሆን አለበት፡፡
- የመለዋወጫ ዕቃው መለያ ቁጥርም በተሽከርካሪው የግል ማህደር ውስጥ ተመዝግቦ እንዲቀመጥ መደረግ አለበት፡፡

5.2.4 <u>የስራ አመረራሩ ምላሽ፣</u>

በተሰጠው አስተያየት መሰረት የምናስተካክል ይሆናል ብለዋል፡፡

6. <u>ልዩ ልዩ፣</u>

6.1.1 <u>ግኝት፣የግንባታ ሥራዎች በመዝገብ ያልተመዘገቡ ስለመሆኑ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል (ሀ) የመንግሥት መ/ቤቶች ያከናወኑዋቸውን የግንባታ ሥራዎች እንደ ቋሚ ንብረት በተለየ መዝገብ መመዝገብ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በዩኒቨርስቲው የሚገኙ ግንባታዎች አለመመዝገባቸው ተረጋግጧል፡፡

6.1.2 <u>ስጋት፣</u>

ለግንባታዎች የተደረገውን ጠቅላላ ወጪ በመነሻነት ወስዶ የእርጅና ቅናሽ ዋጋ ለማሰብ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡

6.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በመመሪያው መሠረት የግንባታዎችን ምዝገባ ማካሄድ ይገባል፡፡

6.1.4 <u>በስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሚመለከተው ክፍል ህንጻዎቹን ኤጀንሲው ባዘጋጀው ቅጽ ግንባታዎቹን እንዲመዘገብ የማሻሻያ እርምጃ እንወስዳለን ብለዋል፡፡

6.2.1 <u>ግኝት</u>፡ <u>የህንፃ ግንባታዎች በተያዘላቸው ጊዜ አለመጠናቀቃቸውን በተመለከተ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ሰኔ/2002 ባወጣው የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 28 ንዑስ ቁጥር 1 መሠረት የመንግሰት መ/ቤቶች የተለያዩ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር ከአቅራቢዎች /ከስራ ተቋራጮች/ ጋር የተደረገውን የውል ስምምነቶች በፍጥነት ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ ይኖርባቸዋል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ ዩንቨሪሲቲው የግንባታ የውል አፈጻጸም ሲታይ፣

- ኢኒቶሪያል እንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን በተባለው ኃ/የግ/ማህበር የሚከናወነው ማዕከላዊ መጋዘን፤ የተማሪዎች ካፍቴሪያ፤ የጥበቃ ቤትና የልብስ ማጠቢያ በውል ስምምነት

የተወሰነው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና ማስረከቢያ በ23/12/2008 ዓ/ም ቢሆንም የግንባታው ሥራ ደረጃ /Physical Status/ 77.71 % መሆኑ፣

- ያሬድ ስዩም በተባለዉ ህንጻ ተቋራጭ የሚከናወነው ሴሚናርና ላቦራቶሪ በውል ስምምነት የተወሰነው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና ማስረከቢያ በ24/4/2008 ዓ/ም ቢሆንም የግንባታው ሥራ ደረጃ /Physical Status/ 77.96 % መሆኑ፣
- ምዕሾ በተባለው ህንጻ ተቋራጭ የሚከናወነው የአጥር ሥራ በውል ስምምነት የተወሰነው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና ማስረከቢያ በ08/9/2008 ዓ/ም ቢሆንም የግንባታው ሥራ ደረጃ /Physical Status/ 10% መሆኑ፣
- ዩናይትድ በተባለዉ ህንጻ ተቋራጭ የሚከናወነው የተማሪዎች ካፍቴሪያ፣ የፕሬዝዳንትና የም/ፕሬዝዳንት በውል ስምምነት የተወሰነው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና ማስረከቢያ በ30/4/2008 ዓ/ም ቢሆንም የግንባታው ሥራ ደረጃ /Physical Status/ 27% መሆኑ፣
- ሐዲሽ ተክሌ በተባለው ህንጻ ተቋራጭ የሚከናወነው የዶሪሚተሪና ላውንደሪ በውል ስምምነት የተወሰነው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና ማስረከቢያ በ30/3/2008 ዓ/ም ቢሆንም የግንባታው ሥራ ደረጃ /Physical Status/ 39% መሆኑ፣
- አበበ ሙሉጌታ በተባለው ህንጻ ተቋራጭ የሚከናወነው የዶረሚተሪ በውል ስምምነት የተወሰነው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና ማስረከቢያ በ24/3/2008 ዓ/ም ቢሆንም የግንባታው ሥራ ደረጃ /Physical Status/ 10.50% መሆኑ፣
- ሸዋዬ በቀለ በተባለው ህንጻ ተቋራጭ የሚከናወነው የአስተደዳርና መምህራን ከፍቴሪያ በውል ስምምነት የተወሰነው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና ማስረከቢያ በ30/3/2008 ዓ/ም ቢሆንም የግንባታው ሥራ ደረጃ /Physical Status/ 40% መሆኑ፣

በአጠቃላይ ግንባታው በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቀ መሆኑን የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በሰጠው መግለጫ ለማረጋገጥ ተችሏል።

6.2.2 <u>ስጋት፣</u>

የህንጻ ግንባታዎች በከፍተኛ ገንዘብ የሚገነቡና ጊዜ የሚወስዱ በመሆናቸው በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ካልተጠናቀቁ ተጨማሪ ወጪን ሊያስከትሉና በመማር ማስተማሩ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላሉ።

6.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በዩኒቨርሲቲው በመከናወን ላይ ያሉ የህንጻ ግንባታዎች ተጠናቀው ለተፈለጉበት ዓላማና አገልግሎት ለማዋል እንዲቻል ተቋራጮች በውሉ መሰረት ግንባታዎቹን አጠናቀው እንዳያስረክቡ ያደረጋቸውን ምክንያት የህንፃ ተቋራጩ ወይም የአማካሪ ድርጅቱ ድክመት መሆኑን በማጣራት የዩኒቨርሲቲው የበላይ ኃላፊዎች ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡

6.2.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

- የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በተቋሙ ውስጥ የተለያዩ ግንባታዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በግንባታው ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች በሁለት የሚከፈሉ ሲሆን የመጀመሪያው ያልተጠናቀቁ ነባር ግንባታዎች ሲሆን ሁለተኛው አዳዲስ ፕሮጀክቶች ናቸው ፡፡ ያልተጠናቀቁ ግንባታዎች በአጭር ጊዜ ለማስጨረስ ጥሩ አፈጻጸም የነበራቸውን ተመሳሳይ ስራ ሲሰሩ የነበሩ ነባር ስራ ተቋራጮች ማለትም ያሬድ ስዩም ሕ/ሥ/ተቋራጭ፣ ሃዱሽ ተክሌ ሕ/ሥራ ተቋራጭ፤ ሙሉጌታ አበበ ሕ/ሥራ ተቋራጭ እና ሽዋዮ በቀለ ሕ/ሥራ ተቋራጭ የተባሉ ስራ ተቋራጮችን በመምረጥ ለማከናወን ጥረት የተደረገ ቢሆንም ከስራው ሂደት ውስብስብነት አንጻር እንደተጠበቀው በተያዘለት ጊዜ ሊጠናቀቅ አልቻለም፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያትነት ከሚጠቀሱ መካከል የሚከተሉት ዋናዎቹ ናቸው፡፡
- ውላቸው የተቋረጠባቸው ስራ ተቋራጮች የግንባታ ስራዎቹን በጊዜ ለማስረከብ ፈቃደኛ ያለመሆን ስራውን ከሚያከናውነው ስራ ተቋራጭ ጋር ርክክብ ለመፈጸም መዘግየትን ፈጥሯል፣
- ቀድሞ ሰዎቹን ሲያሰራ የነበረው አማካሪ ድርጅት የውለታ ጊዜ በማብቃቱ ሌላ አማካሪ ለመተካት ጊዜ በመውሰዱ፣
- አዲስ የተቀጠረው አማካሪ ድርጅት ቀድሞ ከነበረው አማካሪ ጋር ርክክቡ በታሰበለት ጊዜ ያለመከናወን፣
- ተጨማሪ የስራ ትእዛዝ መኖር፣
- የግንባታ ማቴሪያል የማጽደቅ ሂደት በመዘግየቱ፣
- በሁለተኛው ደረጃ አዳዲስ የግንባታ ስራዎች ሲሆነ እነዚህም በኢኩኤተር ኢንጁነሪንግ፤ በዩናይትድ ኮንስትራክሽን እና በምዕሾ ይብራ ስራ ተቋራጮች

አማካኝነት የሚገነቡ የግንባታ ስራዎች ናቸው፡፡ በነዚህ ስራ ተቋራጮች የሚገነቡ ግንባታዎች ከዘገዩበት ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ዋናዎቹ ናቸው፣

<u>ኡኡኤተር ኢንጂነሪንግ</u>

- ቀድሞ ሰዎቹን ሲያሰራ የነበረው አማካሪ ድርጅት የውለታ ጊዜ በማብቃቱ ሌላ አማካሪ ለመተካት ጊዜ በመውሰዱ፣
- አዲስ የተቀጠረው አማካሪ ድርጅት ቀድሞ ከነበረው አማካሪ ጋር ርክክቡ በታሰበለት ጊዜ ያለመከናወን፣
- ለጋራዥ እና ለስቶር የቦታ ለውጥ መደረጉ እና በዚህም ምክንያት ተጨማሪ የቁፋሮ ስራ በማጋጠሙ፣
- የዝናብ ወቅት ስራውን በመረበሹ፣
- ተጨማሪ የስራ ትእዛዝ በመኖሩ፣

<u>በዩናይትድ ኮንስትራክሽን</u>

- ቀድሞ ሰዎቹን ሲያሰራ የነበረው አማካሪ ድርጅት የውለታ ጊዜ በማብቃቱ ሌላ አማካሪ ለመተካት ጊዜ በመውሰዱ፣
- አዲስ የተቀጠረው አማካሪ ድርጅት ቀድሞ ከነበረው አማካሪ ጋር ርክክቡ በታሰበለት ጊዜ ያለመከናወን፣
- ዲዛይን ክለሳ በማጋጠሙ እና ይህም ተጨማሪ ጊዜ በመውሰዱ፣
- ተጨማሪ የስራ ትዕዛዝ መኖር፣
- የግንባታ ማቴሪያል የማጽደቅ ሂደት በመዘግየቱ፣
- የዝናብ ወቅት ስራውን በመረበሹ፣

<u>ምዕሾ ይብራ ስራ ተቋራጭ</u>

የአካባቢው አርሶ አደሮች ከካሳ ክፍያ ጋር በተያያዘ ስራውን ለማሰራት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ምክንያት ስራው ከተጀመረ በኂላ ለረጅም ጊዜ በመቆሙ፣

ምንም እንኳን የግንባታ ስራዎቹ ከላይ በተጠቀሱ እና በሌሎች ምክንያቶች የዘገዩ ቢሆንም በውሉ መሰረት በአማካሪ ድርጅቱም ሆነ በስራ ተቋራጩ የቀረቡ ምክንያቶችን በማጤን የጊዜ ማራዘሚያ የሚያስፈልጋቸውን ተገቢው የጊዜ ማራዘሚያ በመስጠት አላግባብ ያዘገዩትን በውሉ መሰረት በመቅጣት አስፈላጊውን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል በማለት ገልፀዋል፡፡

6.3.1 ግኝት፣ የስጋት ተጋላጭነት፣

በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ሲታይ የፌደራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 ክፍል 4 አንቀጽ 13 እንደተመለከተው የመንግስት መ/ቤቶች የተቋቋሙበትን ዓላማዎች ለማስፈጸም ዕቅዶችና ዝርዝር የዕለት ተዕለት ተግባራት በማከናወን ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችና የተጋላጭነት ደረጃ ለመለየት የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች በመጠቀም የስጋት ምንጮች ዳሰሳ ማካሄድ እንዳለባቸው የሚገልጽ ቢሆንም በዩኒቨርስቲው የተሰራ አለመኖሩ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

6.3.2 ስጋት፣

በዩኒቨርሲቲው የስጋት ተጋላጭነት ፖሊሲ አለመኖሩ በሀብትና በንብረት አስተዳደር ላይ የላላ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ሊያስከትል ይችላል፡

6.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች ለይቶ ለማወቅና እንዲቀርፍም ብሎም ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ዩኒቨርሲቲው የስጋት አስተዳደር ፖሊሲ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

6.3.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የስጋት ተጋላጭነት ዳሳሳ ጥናት በተሰተን አስተያየት መሰረት 2010 አዘጋጅተናል ብለዋል፡፡

6.4.1 ግኝት፣ የICT አስተዳደር፣

በዩንቨርስቲው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ሲታይ፡-

- የመረጃ ደህንነት አስተዳደር /approved IT security policy to ensure data confidentiality, integrity and availability/ **የሌለ** መሆኑ፣
- የአይ ሲቲ ቀጣይነት እና የመልሶ ማቋቋም ዕቅድ /disaster recovery plan/ **የሌለ** መሆኑ፣

በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

6.4.2 ስጋት፣

- ዩኒቨርሲቲው የመረጃ ደህንነት አስተዳደር /security policy/ **ከሌለው** የመረጃዎች ደህንነት ላይኖር ይችላል፡፡

- የአይ ሲቲ ቀጣይነት እና የመልሶ ማቋቋም ዕቅድ /disaster recovery plan/ ከሌለው አጠቃላይ የመስሪያ ቤቱን መረጃ በአንድ ቋት ማግኘት የማይቻልና መረጃች ቢጠፉ/ back up/ ስለማይኖር መተካት የማይቻል መሆኑ፣

6.4.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው የአይ ሲቲ አገልግሎትን የተሟላ ለማድረግ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን ማሟላትና አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል።

6.4.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- የመረጃ ደህንነት አስተዳደር /IT Security Policy/ በተመለከተ ከዚህ በፊት በአይ ሲቲ ተዘጋጅቶ በንድፍ ደረጃ የICT Policy ያለ ሲሆን፣ ይህ የፖሊሲ ዶክመንት የመረጃ ደህንነትም የሚያካትት ስለሆነ በባለሙያ አስገምግሞ ወደ ስራ እንዲገባ ሲደረግ ያለው ስጋት ይቀረፋል።
- የICT Disaster Recovery በተመለከተ እስካሁን ባለው አሰራር ብዙም ከፍተኛ ጭነት ያላቸው ሲስተሞች ስለሌሉ በቢሮ ማሽኖች ላይ ማኑዋል ባክአፕ የሚወሰድ ሲሆን ችግር ባጋጠመ ጊዜ ከነዚህ ማሽኖች አስፈላጊው ዳታ መልሶ ማግኘት ይቻላል። ይህ የተማከለ ዘላቂ መፍትሄ አይደለም ወደፊት ለዚህ ስራ አንድ ሰርቨር የሚዘጋጅ ሲሆን ከተቻለ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር ሰርቨር በነሱ ዳታ ማዕከል በማስቀመጥ ለነሱም ተመሳሳይ አገልግሎቶች በኛ ዳታ ማዕከል በማስቀመጥ ችግሩን ለመፍታት ይሞከራል በማለት ገልፀዋል።

6.5.1 <u>የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ላይ እርምጃ አወሳሰድ፣</u>

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምስት አንቀጽ 17/3 መሰርት ተመርማሪ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረተ ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው። የወሰዱትን እርምጃ እና ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው። በዚሁ መሰረት

ዩኒቨርሲተውን በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምጃ ስለመወሰዱ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች በግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ግዥ የፈጸመ ቢሆንም ነገር ግን አቅራቢ ድርጅቶቹ በጨረታ ያሸነፉት ንብረት በገቡት ውል መሠረት ገቢ ያላደረጉ መሆኑ ተረጋግጠዋል፡፡ ስለሆነም በግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት አዘግይቶ ላቀረቡ ድርጅቶች ቅጣት ሳይፈፀም ብር 332,443.84 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች መኝታ አገልግሎት የሚውል የብረት ቁም ሳጥን ለመግዛት ጨረታ ያወጣ ቢሆንም በጨረታው ሰነድ ላይ ከተገለጸው ስፔሲፍኬሽን ውጭ በብር 4,485,000.00 የእንጨት ቁም ሳጥን ግዥ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

6.5.2 <u>ስጋት፤</u>

በኦዲት ሪፖርቱ ላይ እርምጃ ባለመወሰዱ ምክንያት ኦዲተሩ የውስጥ ቁጥጥሩና የአሰራር ስርዓቱ ላይ አሜኔታ እንዳይኖረውና ለተጨማሪ ብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡,

6.5.3 <u>**የማሻሻያ ሀሳብ፤**</u>

በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲቀረፍ ብሎም ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር በኦዲት በሚሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት በአስቸኳይ የእርምት እርምጃ በመውሰድ የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይገባል፡፡

6.5.4 <u>**የስራ አመራሩ ምላሽ፤**</u>

- አዘግይቶ ላቀረቡ ድርጅቶች ቅጣት ጉዳዩ ለህግ ክፍላችን ቀርቧ በህግ ላይ ይገኛል ፡፡
- ይህ የሎከር ግዢ በተለያዩ አካላት በስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በግዢና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ እንዲሁም በዋና ኦዲተር ኦዲት ተደረጎ ጉዳዩ በህግ የተያዘ ነው ፡፡

በማለት ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የስራ ትብብር እናመሰግናለን!